# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

**ለሰፊው ሕዝብ**
**(ወዛደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር፣)**
**መብትና ጥቅም**
**የሚታገል ጋዜጣ**

ቁጥር 74* ታህሣሥ 29 1973


## ብሄራዊ ነፃነት ቢደፈር !!

ይዘት ገጽ


1. መግቢያ
   ሀ/ ለብሄራዊ ነፃነትና ለህዝባዊ አርነት የተደረገ ትግል .... 2
   ለ/ አዲሱ ፀረ ብሄራዊ ነፃነትና ፀረ ህዝብ ሃይል ......... 3

2. የሩስያ ተስፋፊ መንግሥት ወደ ሃገራችን መግባት
   ሀ/ ከየካቲት በፊት ................................ 4
   ለ/ ከየካቲት ወዲህ ................................ 5
   — የሶቭየት ህብረትና የኩባ ወረራ ................. 5
   — የሩስያ ተስፋፊ መንግስት በሃገራችን ስር መስደድ .... 8

3. የሩስያ ተስፋፊ መንግሥት ወታደራዊ ተፅዕኖና ቁጥጥር ........ 9

4. የሶቭየት ህብረትና የአጋሮቿ የኢኮኖሚ ቁጥጥርና ዘረፋ ....... 15
   ሀ/ የጦር ዕርዳታ ............................... 15
   ለ/ የኢኮኖሚው ግንኙነትና ቁጥጥር ................... 16

5. በሃገሪቱ የውስጥና የውጭ ፖለቲካ ላይ የሶቭየት ህብረት ቁጥጥር.. 20
   ሀ/ የሩስያ ተስፋፊዎች መግባትና የአብዮታችን መቀልበስ ....... 20
   ለ/ የተሟላ የፖለቲካ ቁጥጥር ........................ 21

6. ማህበራዊና ባህላዊ ተፅዕኖ .............................. 23

7. አቋማችን አንደገና
   1. ብሄራዊ ነፃነት ................................. 24
   2. የብሄረሰብ ጥያቄና የእርስበርሱ ጦርነት .............. 25
   3. ፍትህ፣ ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብት ................ 26
   4. የዘቀጠና የደቀቀ የኑሮ ሁኔታ፣ ረሃብና ችግር ......... 26
   5. የትግል አንድነት ጥሪ ........................... 27


---

* ይህን ቁጥር ለዕትመትና ለስርጭት ስንል ለሁለት ከፍለን አውጥተነዋል:: የመጀ
መሪያው ክፍል ከቁጥር 1 እስከ 3 ያለው ሲሆን ፣ ሁለተኛው ከ4 — 7 ያለው
ነው:: ———xxxxxxx———xx——



ክፍል አንድ

## ብሄራዊ ነፃነት ቢደፈር!

### 1. መግቢያ

መኢሶን ገና በመጋቢት 1969 ዓ.ም. "ተስፋቸውን በውጭ ሃይሎች
ላይ መጣል ያመጣን ዕለት ፣ የተኮላሸ አብዮትና 'ከነፃነት ለዘላለም ትኑር'
የተባለቸው አገራችን ተመልሳ ከባርነት ስር የምትወድቅበት ቀን እንዳመጣ ማገ
ዛቸን እንደሆነ መታወቅ አለበት" /ሰህዶ ቁ.53/ ሲል አስጠንቅቆ ነበር::
ይህ የፀና አቋሙን ገልፅ ያደረገበት ቢሆንም፣ ትህትና የተመሰበት ለዘብተኛ
አነጋገርም ይመስል ነበር:: ጉዳዩ ግን የትህትናም የለዘብተኝነትም አንዳይደ
ል ደግሞ የታወቀ ነው:: አስተዋይና ብልህ የሆነ ግንም አብዮታዊ የፖለቲካ ዱ
ርጅት የሚያደርገው ነበር:: በተለይ ደግሞ እንደ መኢሶን ያለ ፣ ሳይንሳዊ
የትግል ዘዴን የራሱ ያደረገ ወዛደራዊ የፖለቲካ ድርጅት ከዚህ የተለየ ሊያደ
ርግ አይችልም:: አይገባውም ነበር:: የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ በዕቅቱ ከገነባ
ር ቀደም ጠላቱ ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና ሎሌዎቹ ጋር አብዮታዊ ትንንቅ ላ
ይ ስለነበር፣ መኢሶን አብዮታዊ ታክቲኩን ተንተርሶ ሁሉንም እንደየአመጣጣቸው
መታገል ነበረበት:: የኢትዮጵያ ሰጋ አብዮት ጠላቶችን እየነጠለና እየከፋፈለ
መምታት ነበረበት:: ነገር ግን ሁሉም አንዲት ጉዳይ ነበረች:: እንደዛሬው
ብሄራዊ ወኔያቸው ሳሽቆ ወደ ዘመናዊ ባንዳነት ከማዘቅዘቃቸው በፊት የጊዜው
የፖለቲካ ተቀናቃኞቻችን፣ መቼም ኢትዮጵያዊ ነበሩና ከማንም ኢትዮጵያዊ ዜጋ
የሚጠበቅ ብሄራዊ ወኔ ይኖራቸው ይሆናል ብሎ በመገመት፣ መኢሶን በጥሞና መገ
ራቱም ጥሩ ነበር:: የሩስያ ተስፋፊዎችን በሚመለከት ግን ፣ የታላቁን የጥ
ቅምት ሶሽያሊስት አብዮት ድሎች ቀልበሰውና ታላቅና ሶሽያሊስትየነበረቸውን ሶቭ
የት ህብረት አዘቅጠው ወደ ኢምፔሪያሊስትነት ደረጃ ያቀረዱ ፀረ ጭቁን ህዝቦች
መሆናቸውን መኢሶን ያኔም ቢሆን አሳጥቶም:: ያም ሆነ ይህ፣ መኢሶን መቼም ቢ
ሆን ደግሞ፣ ኢትዮጵያ ህዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ሆና የምታብበው፣ በራሷ ታጋይ ህ
ዝቦችና ሃብት እንጂ በውጭ ሃይል ላይ ተስፋቀን ጥሎ እንዳልሆነ፣ ኢትዮጵያ የ
ምትገነባው ብሄራዊ ወኔያቸው በሳሳጠቀ ለማንም ማገደዱን በሚገውቁ በልበሙሉዎ
ቹ ሃቀኛ ተራማጅ ልጆቿ፣ በዲሞክራቶቿ በአገር-ወዳድ አፍቃሪያኖቿ ዕጅ እንጂ፣
ለማንም በዕጅ አጉንበስ እንዳልሆነ የፀና አቋሙን ሲገልጽበት የቀረበት ጊዜ
አልነበረም::

"ብሄራዊ ነፃነታችንና መኢሶን" በሚል ርዕስ፣ በሰህዶ ቁጥር 73
እትማችን ውስጥ ፣ በዚያን ወቅት መኢሶን ያካሄደውን የተወሳሰበ ትግል አውስ
ተናል:: ዛሬ አፍጦና አግጦ በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ የመጣባቸው የሩስያ ተስ
ፋፊዎች የባዕድ ሃይል ከገፋና ነጠባጭ ሁኔታው የመጀመሪያ ደረጃ ጠላት ከአደ
ረገው ደግሞ፣ ይቅርታ የሌለ አብዮታዊ ትግል ማካሄዱንም መኢሶን ያውስበታል::
በዚሁ ዕትማችንም በጉዳዩ አንደገና የተመለሰንበት ብሄራዊ ነፃነታችን እንዴት
እንደተደፈረ በዝርዝር ለማሳየትና መኢሶን ደጋግሞ ያሰማውን ብሄራዊ ጥሪ ለማ
ደስ ነው::

የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ደባ ተመቶ ከኢትዮጵያ ከተባረረ ወዲህ
በርሱ እገር ለመተካት ያኔ ያነፍንፍ የነበረው የሩስያ ተስፋፊዎች መንግስት ዛ
ሬ ብሄራዊ ነፃነታችንን በጠማው ረግጦ በአገራችን ላይ ተንሰራፍቷል:: ሃገራች
ንን ሽጠውና ብሄራዊ ነፃነታችንን አስደፍረው ዕድሜያቸውን ለማራዘም የሚጥሩ
ዘመናዊ ባንዳዎች ተከስተውብናል:: እኛም ሃቀኛ ተራማጆች፣ ዲሞክራቶች፣ ሃገ
ር ወዳዶችና የጭቁን ብሄረሰብ ታጋዮች ዕጅ ለዕጅ ተያይዘን ሰፊውን ህዝብ በ
ማስተባበር፣ ይህን አዲስ ፀረ-ብሄራዊ ነፃነትና ፀረ- አብዮት ተስፋፊ ሃይል
ከነሎሌዎቹ ደባቅ ለመምታት በቆራጥነት መታገል የሚኖርብን ሁኔታ ውስጥ ገብተ
ናል:: ከእንግዲህም በውድ አገራችንና በህዝቦቻችን ላይ አዲስ የመጣበት ተስፋ
ፊ ሃይል ሊጋለጥ ይገባዋል:: የጋራ ተግባራችንን ልናነባበት ይገባል::

አገርና ወገን ወዳድ ሁሉ ብሄራዊ ነፃነቱ እንደምን እንደተደፈረ
ተረድቶ፣ ለነፃነቱ ለክብሩና ለኩራ ህልውናው በማለት ዕጅ ለዕጅ ተያይዞ ከል

ተነበ ገን፣ ይህች ውድ ሃገራችን እንደዘረው ዘመን የተስፋፊዎችና የጣልቃገቦች
መናኸሪያ፣ የጥቂት ዘመናዊ የሃገርና የወገን ደሳሎች ማጉሪያና መፈንጪያ፣ የ
ብዙሃን ቢሕልና የሃያሳን መንግሥታት መፈለሚያ ሆና ትቀራለች:: እና ከትውልድ
ትውልድ በብሔራዊ ነፃነታችን ኩራትን የኖርነው አገር—ወገን ወዳጆች፣ ዲሞክራ
ችና ሃቀኛ ተራማጆች ፣ ውስጥ ለውስጥ ከመብሸትሸቅ በሸገር ወደ ጋራ— አምባ
ተኛነት እንድንሸጋገር ሁኔታዎች ሁሉ አጥብቀው ይጠይቁናል:: ተደራጅተን የምን
ገነው ነፃ፣ ሃቀኛ፣ ተራማጅና ዲሞክራቲክ የፖለቲካ ድርጅቶችና የብዙሃን
እንቅስቃሴዎች ይህን የተቀደሰ ትግል አስተባብረን ልንመራው እንችል ዘንድ መ
ተበበራችን የግዴታ መሆኑ ግልጽና የማይታለፍ ጉዳይ ሆኖ ቀርቧል:: መሆኑን
ዘረመ አንደገናና ለወደፊቱም ደግሞ ደጋግሞ በብሔራዊ ጥሪውን የሚያስተጋባው ከ.
ዘሁ መሰረታዊ ግብ ላይ ለመድረስ ነው::

* * *

## ሀ/ ለብሔራዊ ነፃነትና ለህዝባዊ አርነት የተደረገ ትግል

የሃገራችን የጂኦግራፊ አቀማመጥ፣ የምድራችን ሃብትና ለምለምነት፣
የህዝባችን ታታሪነትና ብሩህነት በየጊዜው የተነሱትን ሃያልና ተስፋፊ መንግሥታ
ት ሁሉ በኢትዮጵያችን ምድር ላይ አንግዓያተኩሩ ቢያደርጋቸው ኖሯል::ይህች ውድ
ሃገራችንን ፣ ቢሆንለት በቀጥታ ወረራ የቅኝ ግዛቱ ለማድረግ፣ ካልሆነለትም በ
እጅ አዙር ሊገዛት ያልቋመጠ አንድም ሃያል መንግሥት አልነበረም:: በሰፊው ከ
ፍለ ዘመን እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ኢጣልያን ኢትዮጵያን ለመቃረጥ የቋመጡት ዋና
ዋናዎቹ ነበሩ:: ጣልያን ካንዴም ሁለትና በስቱ የወረራ ጦርነት ከፍታብናለች::
የዛሬዎቹ ዘመናዊ ዛሮች ነም አያቶቹ — የቀደምዎቹ ዛሮች ባይቀሩ ሁሉ ይህችን
ውድ ሃገራችን ከሌሎቹ ጋር ለመቃረጥ የቋመጡበት ጊዜ ነበር:: ያም ሆነ ይህ
ገን፣ የኢትዮጵያ ጀግና ህዝቦች እንቧን ለነርሱ ቀርቶ ለማንም አልበገሩም:: ደ
ጋግሞ ጦርነት የከፈተችብንን ጣልያንን በዱል አያመቱ አበረቁል:: ከአዱዋ ጦር
ነትና ከአርባ ዓመታት በኋላም፣ የጣልያኑ ፋሽስት መንግስት አገራችንን እንደ
ገና ለመድፈር ቢያጣውም፣ የኢትዮጵያ ጀግናና አገር ወዳድ አርበኞች በተሰመደው
ልበሙሉነት በየዱር ገደሉ ተበማርተው ተናንቀውታል:: ከአምስት ዓመት የአርበኝ
ነት ጦርነት በኋላ፣ ወራሪው የፋሽስት ጦርን ከነባንዳዎቹ ደምስሰው፣ በኢትዮጵ
ያ ሸለቆዎችና ተራሮች ላይ ሁሉ 'ጉሮ ወሸባዬ'አያሉ የብሔራዊ ነፃነትን ችቦ ለ
ማብራት ችለው ነበር::

ነገር ግን ደግሞ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ አገሪቱ ያበቀለቻቸው ዲ
ሞክራቶች፣ አገር—ወገን ወዳጆችና አጋሮች ለነፃነትና ለብሔራዊ ክብር መንገዚ
ም የተጣጧትን ያህል፣ ለሥልጣን ለግል ጥቅም ለከንቱ ክብር መገበና ውዳቢ
ሀሊናቸውን የሚሸጡ ከሃዲና የሃገር— ወገን ደሳሎችም ከውስጡ በቅሰውበት ታሪ
ካችንን ያጉደፉ አልጠፉም:: ከፋሽስቱ ጣልያን ጋር ተሰልፍ ኢትዮጵያን የወጋት
ባንዳ ጥቂት አይደለም:: ኢትዮጵያዊ ወኔያቸው ላሸቀ፣ ብሔራዊ ነፃነታችንን
ለአዲሱ ተስፋፊ የሩስያ መንግሥት ሸጠው በቅጥ መንግሥትነት የሚያ ገለግሉት
የዘመኑ ባንዳዎችም የሚደገሙት ይህንኑ ታሪክ እንጂ አዲስ ነገር አይደለም::

ሆኖም ግን ደግሞ፣ በብሔራዊ ነፃነት የትግል ጉዳና ላይ ሺህ ባንዳ፣
ሺህ ደላላ፣ ሺህ ፍርፋሪ ለቃሚ ቢፈለ የማታ ማታ የዱሉ ባለቤት የሚሆነው የታ
ጋዩ አርበኛ ወገን መሆኑ ከቶም አያጠራጥርም:: ታሪክ ደጋግሞ ያሳየው ነው::

ከፋሽስቱ ጣልያን ወረራ በኋላ፣ በመጀመሪያ በእንግሊዝ፣ ከዚያም በ
አሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የሚመራው የምዕራብ ኢምፔሪያሊዝም አገራችንን በዕጅ
አዙር ቅኝ ግዛትነት ይዞ ፈንጭቶ ነበር:: ይሁንና፣ የየካቲቱ 1966 ዓ.ም.
ህዝባዊ አብዮታዊ ማዕበል ቢነሣ ደግሞ፣ የምዕራብ ኢምፔሪያሊስቶች ለዓርበ ዓ
መታት አቅፈውና ደግፈው ያቆሙትን ሥርዓት እንደካርታስ ቤት ደርምሶታል::

የየካቲትን አብዮት በተከተሉት ሰባት ዓመታት የኢትዮጵያ ወዝአደሮች፣



አርበአደሮች፣ አገር ወዳድ መለዮ ለባሾች፣ አብዮታዊ የብዙሀንብ እንቅስቃሴዎች፣
ታጋይ ወጣቶችና ሴቶች፣ ዲሞክራቶችና አገር ወዳጆች በተለያዩ መልኮች የተከሰቱ
በቸውን የጋራ ቀዓሚ ጠላቶቻቸውን ተናንቀው ታላላቅ ህዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ድሉ
ችን ተጎናጽፈዋል:: ኢትዮጵያችንም በብሔራዊ ነፃነት ባዕም የደመቀ ብሩህ የ
ታሪክ ገፅችን ለመፃፍ የተዘጋጀች መስላ ነበር:: እውነተኛ ብሔራዊ ነፃነትና
ህዝባዊ አርነት ፈንጥቆበት ነበር:: ይሁንና ድሉቹ የተፀፈበት ቀለም ሳይደርቅ፣
ከመጋቢት 1969 ጀምሮ የብሔራዊ ነፃነታችን ጥያቄ እንደገና በዓስ ቀርቦ ነ
በር:: ያሁኑ ፀረ ብሔራዊ ነፃነት ሃይል ግን ከቀደምዎቹ ሁሉ ፈጽሞ የተለየ
ነበር::

## ለ/ አዲሱ ፀረ ብሔራዊ ነፃነትና ፀረ ህዝብ ሃይል

እንደናው 'አብዮት' እንደናው 'ሶሺያሊዝም' የሚል፣ በ'ወዝአደራዊ
አለም አቀፋዊነት'ና 'በሶሺያሊስት ወንድማማችነት' ስም እየነገደና እየተመፃደ
ቀ ብሔራዊ ነፃነትን የሚደፍር፣ ለጋ አብዮቶችን የሚበረብርና በመጠረቸም የሚ
ያኮላሽ ነው:: በመሆኑም፣ ያሁኑ የብሔራዊ ነፃነታችን ተቀናቃኝ ልዩና አደገኛ
ነው:: ይህም፣ የታላቁ የጥቅምት ሶሺያሊስት አብዮት ድሉችን ቀልብሶ፣ ታላላቆ
ቹ የወዝአደር መሪዎች የገነቡትን ሶሺያሊዝም ከሥረ መሰረቱ በርብሮ፣ አለም አ
ቀፋዊ የኮምኒስት እንቅስቃሴ መመሪያ የሆነው ማርክሲዝም— ሌኒንዝምን በርዝና
ከልብ በአለም አቀፍ ደረጃ የሶሻሊዝምን ስምና ዝና ያጉደፈ፣ በመሰረታዊ ይ
ዘቱ ከኢምፔሪያሊዝም ያልተለየው የዘመኑ ዛሮች— የሩስያ ተስፋፊና ጣልቃ ገብ
መንግሥት ነው::

ስለሆነም፣ በሶቭየት ህብረት በስም እንጂ በገቢር ሶሺያሊስት መሆን ካ
ቆመች አመታት አልፈዋታል:: ሶቭየት ህብረት በመሰረቱና በገቢር ኢምፔሪያሊስ
ት የሆነች ሃያል መንግሥት ሆናለች:: ሶሺያሊስት ያልሆነና ሃያል መንግስት ደ
ግሞ በወጭ ፖሊሲው በምንም አይነት ሁኔታ ወዝአደራዊና ዓለም አቀፋዊ ሊሆን
አይችልም:: በመሆኑም፣ የሩስያ ተስፋፊዎች መንግሥት በዓለም አቀፍ ደረጃ ወ
ታደራዊና ኢኮኖሚያዊ አካባቢዎችን ለመቆጣጠር ከሌሎች ሃያል መንግሥቶች— በተ
ለይም ከአሜሪካን ጋር በከፍተኛ ውድድርና ፉክክር ውስጥ የሚገኝ መንግሥት ነው::
የውጭ ፖሊሲው ዋና መመሪያ፣ በየጊዜው እየሰፋ የሚሄዱ አካባቢዎችን በርሱ ተፅ
ዕኖና ቁጥጥር ሥር ማዋል እንጂ፣ የህዝቦች አብዮት፣ ነፃነትና ክብር አይደለም::
የሩስያ ተስፋፊዎች መንግሥት በሸንጉ አገር ውስጥ ለራሱ ያደረ ነውስ ከበርቴዎችን
ቢሮክራሲያዊ ከበርቴዎችን፣ ወይንም እንደርሱ በነማርክስና በነሌኒን ስም የሚነግ
ዱ ጥቂት ከሃዲያንን ዕድ ካስገባና የሚፈናጠጣቸው አስከአገኘ ድረስ፣ እነዚህም
የርሱ ጠማ ላሽ ሁነው በአሽንጉሊትነት — በቅጥ መንግሥትነት ከአገለገሉት፣
ህዝቦች በአርስ በርስ ጦርነት ቢተላለቁና ዕጣቸው በሚሊዮን መሰደድ ቢሆን፣
ሃገሮች በወታደራዊ አምባገነን አገዛዝ ታፍነውና ተረግጠው ቢገዙ፣ በኑሮአቸው
ቢማቅቁና በረሃብ ቢረገፉ ደንታ የለውም:: ፍላጎቱ፣ ከምዕራብ አገሮች ጋር ለ
ዕውነተኛ ነፃነታቸው የሚታገሉ ህዝቦች መካከል "በዓለም አቀፋዊነት ድጋፍ"
ስም በርጉ መግበትና፣ አገሮችንና ህዝቦችን በርሱ ተፅዕኖ ሥር ለማጠቃለልና
ለመመዝበር ነው:: ለዚህም፣ በደቡብ አሜሪካ ኩባ፣ በአፍሪቃ አንጎላና አገራ
ችን፣ በእዝያ ቬየትናም፣ ካምፑችያ፣ ላኦስና አፍጋኒስታን፣ በቅርብ ምስራቅ
ደቡብ የመን ቁጣባጭ የሆኑ ምሳሌዎች ናቸው:: ከዚህም ሌላ በሶቭየት ህብረት
ሥር የሚማቀቁት ራባቸው የምሥራቅ አውሮፓ ህዝቦች አሉ:: ከዚሁ በተያያዘ፣
ፍላጎቱ አገሮችን በተፅዕኖውሥር ለማጠቃለልና ሃያልነቱን በዓለም አቀፍ ደረጃ
ለማንገሥ የሆነ መንግሥት፣ የግዴታ ተስፋፊ፣ የግዴታ ጣልቃ ገብ መንግሥት ይ
ሆናል:: አልፎም በዕብሪቶች በተመሳው "የእኔ አውቅላችኋለሁ" ፖሊሲው ወደ ዘ
ረኝነት ጭምር ይጠጋል:: ህዝቦችን ረግጦ ለመግዛት፣ ለስቃይና ለግፍ ዓርጉ
የበላይነትን ለማፅደቅ ይገደዳል::

"ይገደዳል"፣ ምክንያቱም አንዱ ተስፋፊ መንግሥት ዓለማው አንዱን
አገር በቁጥጥሩ ሥር አውሎ በኢኮኖሚ በመመዝበር፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚያ
ደርገው ትንንቅ መሣሪያ ለማድረግ ከሆነ፣ ይህ ፍላጎቱ የግዴታ ከሃገሪቱ ህዝ

ብ ፍላጎት ጋር ይጋጫል:: አንዱ ህዝብ ደግሞ አብዮታዊ ትግል የሚያካሂደው ፣ ደርቦ መታገል አምሮት ባይሆን፣ የውስጥም ሆነ የውጭ የብዝበዛና የጭቆና ቀንበር ለመጣል ነው:: ይህንን ዓላማ ከሥራ ላይ የሚያውል ህዝባዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ብሄራዊ የሆነ መንግሥት ለማቋቋም ነው:: የአብዮት ግብ መምታትና የእንደዚህ ዓይነቱ መንግሥት መቋቋም፣ ከፋሽስቱም ሆነ ከሌላ ተስፋፊ ዓላማ ካለው መንግሥት ጋር ሙሉ ለሙሉ ይፃረራል:: የፋሽስቱ ተስፋፊዎች፣ጥቅማቸውን ሆነ ዓለም አቀፋዊ አስትራተጂያቸውን ከሥራ ላይ ለማዋል ህዝባዊ ባይሆን፣ አገሩንና ወገኑን ከድቶ ለነሱ ጥቅም ያደረ፣ ዲሞክራሲያዊ በይሆን እነሱው ዕዓ በዕዓ እየነከሩ በሚሰጡት መሣሪያ ህዝብ በፈለጉ ፍራቻነት የሚገዛ አምባገነናዊና ቅምጥ መንግሥት ይፈልጋሉ:: በሌላ በኩል ግን፣ የህዝብ ድጋፍ ያለው፣ የሃገሩን ብሄራዊ ጥቅም የሚያስቀድም መንግሥት የተስፋፊዎች ፀር እንጂ፣ ተባባሪ አይሆንም:: ለዚህ ነው፣ የፋሽስቱ ተስፋፊዎች ጥቅም መከበር የአብዮትን መቀልበስ ይጠይቃል የሚባለውም:: ለዚህ ነው፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ከመጋቢት 1969 በኋላ እያንዳንዱ ፀረ አብዮትን የሚያጠናክር እርምጃ ሁሉ፣ በዚያው ልክ ብሄራዊ ነፃነታችንን ገደል እየጨመረው የመጣው:: ለዚህ ነው፣ እያንዳንዱ ብሄራዊ ነፃነታችንን በይበልጥ የደፈረ እርምጃ ሁሉ ፣ ከኢትዮጵያ አብዮት መቀልበስና ከብሄራዊ ነፃነቷ መገፈፍ ጋር ተያይዞ የተከናወኑት:: የፋሽስቱ ተስፋፊ መንግሥትና ተቀጥላዎቹ በሃገራችን ላይ የፈጸሙትን የጣልቃ ገብነት ታሪክ ስንመለከት የምንረዳውም መሰረታዊ ሃቅ ይህው ነው::

## 2. የፋሽስቱ ተስፋፊ መንግሥት ወደ ሃገራችን መግባት

### ሀ/ ከየካቲት በፊት

የህንድ ውቅያኖስ፣ ቀይ ባህርና የአፍሪካ ቀንድ በዓለም አቀፍ ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ ስትራተጂ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ አሏቸው:: አብዛኛዎቹ የዓለም ገበያ ሸቀጦች በህንድ ውቅያኖስ ላይ ይመላለሳሉ:: ቀይ ባህር ወደ አውሮፓና ሩቅ ምሥራቅ እስያ ለሚተላለፈው ሸቀጥ አጭሩ የባህር መንገድ ነው:: የዘይት አምራች አገሮች በህንድ ውቅያኖስና በቀይ ባህር ዙሪያ ተራ በተራ ተደርድረው ይገኛሉ:: ወዲህም ደግሞ፣ በውሃ ሃይልና በሌሎች የእርሻና የማዕድን ሃብታቸው የታወቁ ሃገሮች /እንደ ኢትዮጵያ/ የሚገኙት በዚሁ አካባቢ ነው:: በወታደራዊ በፈርነታቸውም አንፃር፣ እነዚህ አካባቢዎች ለማጥቃት ሆነ ለመከላከል፣ ወይንም ለወታደራዊ ስለላና ሎጂስቲክ.... እጅግ አመቺ የሆነ አቀማመጥ አሏቸው:: የጂኦግራፊ ተፈጥሮአቸውና የአየር ባህሪያቸው ሁሉ እጅግ አመቺ ነው::

ስለሆነም፣ የዓለም ሃያላን መንግሥታት፣ ዙሪያችንና ሃገራችንን በተፅዕኖቻቸው ሥር ለማዋል ከፍተኛ ውድድርና ግብ ግብ ሲያካሂዱ ኖረዋል:: ቀደም ቢል የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የበላይነትን ይዞ ሃገራችንን ቁጥር በተፅዕኖው ሥር አድርጎ ይገኝ ነበር:: ይሁንና፣ ሶቪየት ህብረት በዚያን ጊዜም ቢሆን አልተኛችም ነበር:: ከካባቢያችን አገሮች ሊሊ እሚን ባይቀር በግብፅ፣ በሱዳን፣ በሶማሊያና በደቡብ የመን ሃገሮች ላይ ከባድ ተፅዕኖዎችን አሳርፋ ኑራለች:: ከዚህም በሻገር፣ የአፍሪካን ቀንድ በመመለከተው ፣ ገና ከ60ኛው ዓመት ጀምሮ፣ "የአፍሪካ ቀንድ ሃገሮች በዘርና በባህል ተመሳሳይነት አሏቸው" በሚል ሱዳን፣ ኢትዮጵያ፣ ጅቡቲ፣ሶማሊና የሁለቱ የመን ግዛቶች በአንዳች ዓይነት የፌዴራል መንግሥት ሥር ተጠቃልለው በርሷ የበላይነት ሥር እንዲተዳደሩ ታቅዶ እንደነበረ የታወቀ ጉዳይ ነው:: ይህ፣ ሶቪየት ለአፍሪካ ቀንድና ከዚያም በሻገር የተለመቸው "የፌዴራል መንግሥት" እቅድ፣ በሩቅ ምሥራቅ እስያ ለቬትናም —ካምፑቻ — ላኦስ ከተለመቸው እቅድ በምንም አይለይም:: እንዲያውም፣ በስፋት ሆነ በአጠቃላይነቱ እጅግ የላቀ ነው:: አልፎም ወደ ዘረኝነት ተጠግቶ "ለፌዴሬሽኑ" መሰረት የሚያደርገው "ዘርና ባህልን" እንጂ፣ የዓምፕራሊያዊ የሰውዎ መመሪያዎችን እንኳን አይደለም::



ኢትዮጵያን በሚመለከተው በኩል፣ ሶቪየት ህብረት ገና በሃይለሥላሴ ዘመን በብዙ ዘዴ ሥር ለመስደድ ቅምክር ነበር:: ከዚህም አልፋ፣ ለመጭው ጊዜ "ተገንጣዮችን" ታደራጅ ነበር:: በነጋሲው አገዛዝ ሥር ከፊውዳሉ ሃይለሥላሴ ጋር ሶቪየት የነበራትን "የወዳጅነት" ፖለቲካ ማንም ያስታውሰዋል:: "ታላቅ መሪ" "የአፍሪካ አባት"፣ "ዘመናዊው ንጉሥ" ከማለትም አልፋ፣ የነመንግሥቱ ነዋይን የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ፣ "የሃገሪቱን እርምጃ ለማደናቀፍ የቀኝ ሃይሎች የጠነሰሱት ሴራ" በሚል "ኒው ታይምስ" በተባለው ጋዜጣ ላይ አትታ እንደነበረም ይታወቃል:: በጊዜው በነበረው የተማሪ እንቅስቃሴም ላይ ልክ ዛሬ እንደምታደርገው ልዩ ልዩ መበናኪሎችን ታደርግ እንደነበር በጊዜው በሶቪየት ህብረትና በምሥራቅ አውሮፓ ይኖሩ የነበሩ ተማሪዎች ያስታውሱታል:: በኢኮኖሚውም በኩል ሥር ለመስደድ /ጠልቃ ሆስፒታል፣ በባህር ዳር ፖሊ ቴክኒክ፣ በአሰብ ዘይት ማጣሪያ፣ በልዩ ልዩ ሃገሪቱ ፕሮጀክቶች ...ወዘተ አማካኝነት/ ስትቦረቦር ቆይታለች:: የፖለቲካውን በሚመለከተው ደግሞ፣ በዚህ ጊዜ ውስጥ በይበልጥ ያተኮረችው ፣ "ከንጉሡ ሃይለ ሥላሴ በኋላ" ለሚደረገው ትግል ተጠሪዎቿን በማዘጋጀት ላይ እንደነበር የሚያስረዱ በርካታ መረጃዎች አሉ:: ይህንን ጉዳይ በሚመለከተው ወደ መአበን [illegible] ተመልሰን ብናስተውል እንኳን፣ ገና በሃይለ ስላሴ ዘመን "ምን አስፈ/ አንድ አመራር አንድ ሆናችሁ ታገሉ ብትመሰርቱ?" በተባለው እና እንደነበሩት:: "እየተባሉ ከሶቪየት በኩል የተነገራቸው የመኢሶን አመራር አባሎች ጥቂት አልነበሩም:: እነርሱ፣ ደግሞ እንኳን መኢሶንን መሥርተው በህቡዕ በመታገል ላይ ቢገኙም፣ "እኛ ተማሪዎችና ምሁራን ነን... እንዲህ አይሆንም "ቢሉ አበፍሩው መልሰ የተቀዳል:: የፋሽስቱ ተስፋፊዎች ግን፣ የኢህአፓ መሥራቾች ዘንድ ተልኮስከበው የጋለጋለ ሁሉ የኢትዮጵያን አብዮት በአፍላው ላይ እንዴት እንዳሰለቱ የታወቀ ጉዳይ ነው:: በዝርዝር ወደፊት የቀነን ብርሃን ማየት ደግሞ አይቀርም:: እዚህ ላይ ግን የፋሽስቱ ተስፋፊዎች ኢትዮጵያን በቀጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ያበያቸው ዱና ዱና ስራ ላይ ማተኮሩ በቂ ነው::

### ለ/ ከየካቲት ወዲህ

ከ1966 ዓ.ም. ወዲህ፣ አብዮቱና ነፃነቷ በሩሉ ሃቀኛ ተራማጆች ሥር እየሰደደየገፋው የየካቲት አብዮት ፋሽስቱ ተስፋፊና ተጋሪ መንግሥት መገቢያ ቀዓዓ አልከፈተለትም ነበር:: በተቃራኒው፣ አገራችን እውነተኛ ገለልተኛ ነፃ ሃገር እንድትሆን ሃቀኛው ተራማጅ፣ ዲሞክራቲክ ሃገር ወዳድ የተያያዘውን ትግል አፋፍሞ ቀጠለ:: ለዚህ ራሱ የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ሊጠቀስ የሚችል ትልቅ ማስረጃ ነው:: በወቅቱ ስለሬስ መተማመንና በብሄራዊ ነፃነት ጥያቄዎች ላይ የተሰጡትን የትምህርትና የፕሮፓጋንዳ ቅስቀሳዎችን ማስታወስም ይቻላል.....ወዘተ::

ይሁንና፣ በዚሁ ጊዜ ውስጥ ደግሞ፣ ለብሄራዊ ነፃነታችን የሚያበጉ አንዳንድ እርምጃዎች በያኔው የነውስ ከበርቴ የደርግ መንግሥት አልተወሰዱም ማለት አይደለም:: በዚህ አንፃር ከሁሉም በላይ መነሳት ያለበት ጉዳይ፣ ደርግ አንዳንድ አባሎችንና ሌሎችን "ለፖለቲካ ትምህርት" በሚል ወደ መስኮብ መላኩ ነው:: የፋሽስቱ ተስፋፊ መንግሥት በቁጥጥሩ ሥር ሊውሉ የሚችሉ ከሃዲዎችን ለመለመል የቻለውም ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ነበር:: እንደሚታወቀው የጋለጋለ "አብዮታዊ ሰደድ" ተብሎ በወጣው ድርጅት ውስጥ፣በኋላ አሲያ ለገበ አስፋው የሚመራውን ከሃዲና አረመኔያዊ ቡድን በማቋቋም እንደፈለጉ ሊጠቀሙበት ችለዋል::

የፋሽስቱ ተስፋፊና ጣልቃ ገብ መንግሥት የሃገራችንን ብሄራዊ ነፃነት በር ለመበርገድ የበቃው ግን ይልቁኑ አራሱ አስታጥቆና ገፋፍቶ የለቀቀውን የሶማሌ ጦር ድንበራችንን በደፈረበት ወቅት ነው::

#### — የሶማሌ ወረራና ሶቪየት ህብረት

ሶቪየት ህብረት በአፍሪካ ቀንድ ያሉ አገሮችን በሌላ በሌላ ሃይል በቁጥጥሯ ሥር ማድረግን አላማዋ ከአደረገች ብዙ ጊዜዋ ነው:: በሶማሌ በርሷ ቁጥጥር ሥር በነበረችበት ወቅት ኢትዮጵያም ከተደመረች አላማዋ ግቡን ለመምታት ተቃ

ረብ ማለት ነው:: በየሃገሩ የርዕ ቅምጥ መንግሥታት ከተቋቋሙ፣ በርዕ የበላ
ይነት በቅድሚያ ሱማሌ፣ ጅቡቲና ኢትዮጵያን በኃላም ሌሎችን የሚጠቀልል "ፌዴሬ
ሽን" ማቋቋም አይገደም:: ይህ እንዳሆን ግን ኢትዮጵያን በርዕ ቁጥጥር ሥር
ማድረግ የሚያስፈልግ ተገልጿ ነበር:: እንዴት ይሆናል? እርዕ አስታጥቃ·ያበ
ሰጠነችው የሱማሌ ጦር፣ ኢትዮጵያ ገና በአብዮት አፍላ ላይና ከምዕራብ ኢምፔ
ሪያሊዝም ጋር ቅራኔ ውስጥ ባለችበት ወቅት፣ ወረራ እንዲያካሂድ፣ ወረራው ቢ
ገፋ የኢትዮጵያ አብዮትና አንድነት እንዲወጠር፣ የኢትዮጵያ አብዮትና አንድነ
ት አደጋ ላይ ቢወድቅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሷት መልመሎቿ አማካይነት ኢትዮጵያ
ዘቅ ብላ የረስያ ተስፋፊዎች መንግሥትን እጅ እንድትነሳ፣ ብሄራዊ ነፃነቷን
አሥረግጣ እንድትማጠን፣ በበሽየት ሀብረት የበላይ ዓኝነት የሱማሌና የኢትዮጵያ
"ችግር" መፍትሄ እንዲያገኝ፣ በኢትዮጵያና በሱማሌ ቅምጥ መንግስቶች አማካይ
ነት አካባቢውን በዓለም አቀፍ የጦርነትና የምዝበራ ስትራተጂዋ ውስጥ አስገብታ
ሀዝቦቻቸውንና ሃብቶቻቸውን መመዝበር:: የረስያ ተስፋፊዎች መንግሥት ዕቅድ
ይህ ነበር:: ሆኖም ዕቅዱ ሁሉ እንደተተለመው አይገጥምምና፣ የኃላኃላ በሽየት
ሀብረት በሱማሌና በኢትዮጵያ መካከል ምርጫ ማድረግ ተገዓለች:: ኢትዮጵያን
ለወረራ በማጋለጥና በማመቻቸት በሽየት ሀብረት የተጫወተችውን ሚናና ያኔ የነ
በረውን ሁኔታ ከዚህ የበለጠ ገባ ብሎ መመልከቱ ነገሩን ይበልጥ ገልጽ ያደር
ገዋል:: የሁኔታው ሂደት ዘቅ ብለን እንደምናየው ፈጣንና ሤራ የተመላበት ነ
በር::---

እንደሚታወሰው፣ ከመጋቢት 1969 ዓ.ም. አንስቶ፣ የረስያ ተስፋፊዎ
ች የ"ሶሽያሊዝም" ስምንና"የዓለም አቀፋዊ ወዝአደራዊነት" ባንዓራቸውን አን
ገበው ኢትዮጵያን መቅረብ ይጀምራሉ:: የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ከአሜሪካን ኢምፔ
ሪያሊዝምና ከሎሌሎቻቸው ጋር የሞት የሽረት ትንንቅ ሲያደርግ ይልቁንም ከጠላ
ቶቹ ጋር ውስጥ ውስጡን ያልተበሰሬትን ያህል፣ መንገዝም "ከጎናችሁ ነበርን"፣
"አብዮቱን ካልደገፍን ምተን እንገኛለን ይሉ ጀመር:: "በውነትም" ይሉ ገቡ፣
"በውነትም ስለአብዮታችሁ እስከአሁን ያሰወቅነው በዜና እጥረት ምክንያት ነው"
እያሉ፣ ይቅርታ ማለት ቢቀራቸው አፍና ቀታቸውን አጉረፈት....ወዘተ..:: የበ
ሀል መልዕክተኞቻቸውና ልዩ ልዩ አማካሪዎቻቸው በብሄራዊ ቲያትርና በየአብዮት
አደባባዩ ተወናዩ....ወዘተ...:: የበሽየት ሀብረትና የተቀጢላዎቿ ቀንደኛ
መሪዎችም፣ ገና አገራቸው አገራችንን እንደረገጡ፣ የቆየ "የፌዴሬሽን" ህልማቸ
ውን ከሥራ ላይ ለማዋል ያሽቃብጡ ጀመር:: በመጋቢት 1969፣ በኤደን ከተማ
ውስጥ በካስትሮ ሊቀመንበርነት የተካሄደው የሽሉቃ መንግስቱ/ በይድ በሬ ድርድ
ር ዓላማም ይኸው ነበር:: በድርድሩ ወቅት ካስትሮ ከዚህ በላይ ያነበነውን
"የፌዴሬሽን" ሃሳብ ለሁለቱም መሪዎች አቅርቦ "ለማገባበት" ሞከረ:: ሰይድ
በሬም ተቀበለው::

ሰይድ በሬ ሃሳቡን በወቅቱ የተቀበለው፣ "ፌዴሬሽኑ" የሚባለው ነገ
ር "ኢትዮጵያን፣ ኦጋዴንን፣ ሱማሌን.." እንዲያጠቃልል በሚል ነበር:: የረ
ስያ ተስፋፊዎች፣ ይህንን ሃሳብ ያመነጩትና የሚደገፈትም በሆኑ የኢትዮጵያን አ
ምቢታ ለመወጣት ዘዴ መፈለግ ነበረባቸው:: በመሆኑም፣ ባንድ በኩል፣ ሱማሌ
በጦር ሃይል ኦጋዴንን እንድትወርር እንድትይዝ፣ በዚህ መልክ ኢትዮጵያ በተካ
ላካይነት ደረጃ ከተቀመጠች በኃላ የፌዴሬሽኑ ሻብ እንደገና እንዲነሳ ያሤራሉ::
ለዚህም እንዲያመች፣ 14 ዓመት ሙሉ ያስታጠቁትን የሱማሌ ጦር ከመጋቢት 1969
በኃላ በጥድፊያ ስንቅና መሣሪያ እያጋዙ ያጠናክሩት ጀመር:: በሌላው ወገን ደ
ግሞ፣ ኢትዮጵያን ትጥቅ ወደ ማስፈታት ተሸጋግረው "በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተቀ
ነባበረው መረጃችን እንደደረሰነበት" ይሉ ጀመር:: "በማመጡት ወረት ኢዲዩና
ኤርትራዊያን ከግብፅና ከሱዳን ጋር በመተባበር ከፍተኛ የጥቃት ዘመቻ ያደርጋሉ
በሱማሌ በኩል /ስና ይሁንብችሁ// ምንም አደጋ የለም:: ስለዚህ ኦጋዴን ያ
ለው ሜካናይዝድ ጦር ወደ ሰሜን ይሂድ" የሚል ሃሳብ ለደርግ ያቀርባሉ:: እን
ደውነትም ከሆነ፣ ባልቀረው የሱማሌ ወረራ ጥያቄ ልይ በዚያን ጊዜ የታየው ታ
ሪክም እጅግ አስደናቂ ነበር::

ከሃረርጌ የህዝብ ድርጅት ፅ/ቤት የሚደርሱ መረጃዎች ሱማሌ ለወረራ
በመዘጋጀት ላይ መሆኗን ይገልፃሉ:: በጊዜው የፅ/ቤቱ ሃላፊ የነበረው ጓድ
አብዱላሂ ዩሱፍ /በነርሱ ዕጅ በቅድሚያ መስዋዕት የሆነውም ለዚህ ነው/ አንደኛ፣
ያካበበው ጦር እንዲጠናከር፣ ሁለተኛ፣ ህዝቡ እንዲታጠቅ በማለት በተደጋጋሚ ይ
ጠይቃል:: በኃላ ይፋ ወጥቶ የታየው የረስያ ተስፋፊዎች አሻንጉሊት፣ በደርግና
በ"አብዮታዊ ሰደድ" ውስጥ የተቀመጠው የነጭ አለቃ ለገሰ አስፋው ቡድንና አደ
ሃሪው ቢሮክራሲ ግን ምን ይሉ ነበር??

"አደጋ የለም/ መኢሶን ህዝቡ ይታጠቅ እያለ የሚጨቀጭቀው ትጥቅ ለ
መሰብሰብ ነው" ወዘተ.

ምን ይኼ ብቻ/ በሰኔ ወር 1969 ዓ.ም. ከሃረርጌ፣ ከሲዳሞና ከባ
ሌ ህዝብ የተላኩ የገበሬ ማህበራት መሪዎች አዲስ አበባ ድረስ መጥተው፣ የአ
ደጋውን አሳሳቢነት በመግለጽ ትጥቅ እንዲሰጣቸውና መንግሥትም መግዛት ካቃተው
እዋጥተው ወጭውን ለመቻል ዝግጁ መሆናቸውን ሁሉ አስታውቀው ነበር:: ይህም
"የመኢሶን ሤራ" ተብሎ፣ የገበሬዎቹ መልዕክተኞች አዲስአበባ ውስጥ ለብዙ ጊዜ
ቢንከራተቱ ከቆዩ በኃላ ባዶ እጃቸውን ተመልሰዋል:: የደርግ ልቡና በተቃራኒ
ባንድ ወገን ተስፋፊዎች በሚሰጡት መረጃና ማረጋገጫ ተሰልቦ ነበር:: በሌላው
ወገን፣ ለሃገር ጉዳይ ከመጨነቅ ይልቅ መኢሶንን በመፍራትና በመጠራጠር የፀረ
አብዮተኞችን ብበት ማሸተት ጀምር ነበር::

ነገር ግን፣ ለጥቃት በተጋለጠው የምስራቅና የደቡብ ምሥራቅ ድንበር
ዞሪያ በጥቂት ቀናት ውስጥ የጦርነት ደመና አንዣበበ:: የሱማሌ ጦር በየዕለቱ
ሺህ በሺህ እየሆነ ጎረፈ:: የረስያ ተስፋፊዎች "ሱማሌን እንገታለን" እያሉ
ደርግን የሰበኩበት ቃል ነጭ ውሸት ሆኖ የተጋለጠውን ያህል፣ ቢሮክራሲው "ስለ
ሰርጎ ገብ አንዳም ተጨባጭ መረጃ የለም" እያለ የዘራው መረጃ፣ ከባድ የፀረ
አብዮት ተንኮል እንደነበር ገሃድ ሆነ:: ይሁንና፣ ኢትዮጵያ በምን ትከላከል??

የውጋዴኑ የጦር ሃይል በረስያ ተስፋፊዎች ሤራ ወደ ሰሜን ተልኳል::
አብዛኛው ሠራዊት በኤርትራው ጦርነት ተጠምዷል:: በጭሩ፣ ከራሱ ከህዝቡ በስተ
ቀር ሌላ ሃይል የለም:: ህዝቡ "ትጥቅ/ ትጥቅ/" እያለ ይጮሃል:: አድሃሪው
ቢሮክራሲ "የመኢሶን ተንኮል" እያለ ያላዝናል:: ደርግ ህዝቡን ቀስቅሶና አስ
ታጥቆ ማዝመቱን ይፈራል:: የረስያ ተስፋፊዎችና ተቀጢላዎቹ "ታገሱን፣ አቋማች
ንን እናስታውቃለን" እያሉ ጊዜ ለመግዛት አደብተዋል:: ጊዜ የሚገዙት ሃገሪቱ
የበለጠ ተጨናንቃ አገራቸውሥር የምትወድቅበት ጊዜ እስከመጣ ነበር:: የጠበቁ
ትም አልቀረም::የሱማሌ ወራሪ ጦር መድፍና መትረየስ ጅጅጋን ተሻግሮ በሃረር
ና በድሬደዋ ከተሞች ላይ ያጓራ ጀመር:: በዚህ አስከፊ ወቅት፣ ሽንጣቸውን
ገትረው ቢቆዩ የነበሩት፣ በአካባቢያቸው የህዝብ ድርጅት ፅ/ቤት ካድሬዎች እ
የተመሩ ህይወታቸውን የሰውት የድሬደዋ የሲሚንቶና የጥጥ ፋብሪካ ወዝአደሮች፣
የገበሬ ማህበራት ጥበቃ አባላት፣ የአካባቢው ገበሬዎችና ወጣቶች ነበሩ:: ይ
ህን ወደፊት ታሪክ በሚገባ ይገልፀዋል::

የሆነው ሆኖ፣ ኦጋዴን እንደተያዘ አንድ በብርሃኑ ባየህ የሚመራ
የመልዕክተኞች ቡድን፣ "ሱማሌዎችን ገፋፊን እንጂ" ለማለት ወደ በሽየት ሀብ
ረት ሄዶ ነበር:: የሱማሌ መልዕክተኞችም እዚያው ሞስኮ ከተማ ይገኙሉ:: ይ
ሁንና፣ የብርሃኑ ባየህ ቡድን ሞስኮ ከተማ ሆቴል ውስጥ ለአንድ ሳምንት ያህል
ቢቀመጥ፣ እንኳን ብሬዥኔቭና ኮሲጊን ቀርቶ በወጉ የሚቀበለው ሌላ ባለሥልጣ
ን ባያገኝ ይከርማል:: በመጨረሻው ላይ፣ አንድ የውጭ ጉዳይ ባለ ሥልጣን ቢ
ቀበለውም፣"ሱማሌዎችም እዚሁ አሉላችሁ:: በውጋዴን ጉዳይ ላይ ተወያዩ" ብሎ
ከመሸኘት ሌላ የጨመረበት ነገር አልነበረም:: ይህ ቡድን እንደተመለሰም፣ በ
ጠቅላላው በደርግ አካባቢ "በሽየት ሸረሞጠች/" /የተጠቀበው ቃል በቃል ነው/፣
"በመረጃ ስም ጉድ ሠሩን"፣ "ተከላካይነት ደረጃ አውርደውን ተደራደሩ ይሉናል"
የሚለው ትችት በሰፊው ይሰማ ነበር::

ነገር ግን በዚያው ሰሞን ደግሞ፣ ሱማሊያ በበሽየት ሀብረት የተሰጠ
ትን የውጋዴን ገደብ አልፋ መሻገሯና እስከአቃቂ ድረስ ለመዝለቅ የዘረጋችው
እቅድና እንቅስቃሴ ይፋ ወጣ:: የረስያ ተስፋፊዎች ይህንን የሱማሌ እርምጃ /
ማለትም ከውጋዴን ክልል ማለፍ/ በሱማሌ በኩል "ቃል እንደተጣበባቸው" አድር
ገው አቀረቡት:: በአፍሪቃ አገሮችና በዓለም ህዝቦች ፊት ሱማሌን ደግፈው ለ
መቆም እንደማይችሉ ግልጽ ሆነላቸው:: በመጀመሪያ፣ ሱማሌን በዲፕሎማሲ ግን
ኙነቶችና በምክር ለመጪን ሞከሩ:: ከውጋዴን እንዳታልፍ አጥብቀው አሳሰቧት::

ሶማሊ ግን አሻፈረኝ አለች:: የሩስያ ተስፋፊዎችን የማግባበት ሙከራ በተቃራኒ ከህደት እንደተፈጸመበት አድርጋ ቆጠረችው::በጀመረችው ጦርነት ገፋችበት:: "ያልታሰበ" እንበለውና፣ አዲስ ሁኔታ ተፈጠረ::

የሩስያ ተስፋፊዎች በአፍሪቃና በዓለም አቀፍ ፖለቲካ አንፃር ወገን እንዲመርጡ ተገደዱ:: በተፈጠረው ሁኔታ የኢትዮጵያ አቋም በአፍሪቃና በዓለም አቀፍ ፖለቲካ ውስጥ፣ ተደጋፊነት እንዳለው የታወቀ ነበር:: ስለሆነም፣ ፊታቸውን ወደ ደርግ አዞሩ:: "ከተወረረችው ኢትዮጵያ ጉን ተሰልፈን እንገኛለን" በማለት፣ የተጠቁ ህዝቦች ወዳጅነታቸውንም ለፈፉ:: ነገር ግን ውስጣዊ ምክንያታቸው ሌላ ነበር:: ዘር ዘር፣ ከሶማሊና ከውጋዴን ይልቅ፣ የ30 ሚሊዮን ታታሪ ህዝብ ባለቤት የሆነችው ሃብታሟና ለምለሟቷ ኢትዮጵያ ሺህ ጊዜ የበለጠ እንደምታጠጣ በማሰባቸው ነበር::ደግሞም በወረራው ተደናገጠ የሚይዝ የሚጨብጠውን ያጣው ደርግ፣ ከነርሱ ጫማ ሥር ለመውደቅ የተዘጋጀ መሆኑንም አውቀውታል: ቀደምውንም ቢሆን ያሤሩ የነበረት ለዚህ ሁኔታ መፈጠር ነበር:: በመረሳቸው:: እንዳያውም፣ ከዚህ ሌላ በሤራቸው ውስጥ፣ በይዶ በረን ሊያስኩርፍ ለሚችል ሁኔታ ሁሉ የተዘጋጁ ነበሩ:: የበይዶ በረ መንግሥት ያከሄደው ወረራ ከከሸፈ ወዲህ የተመከረበት መፈንቅለ መንግሥት የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው:: የሩስያ ተስፋፊዎች ዕቅድ በዚያም ሆነ በዚህ፣ በሶማሊና በኢትዮጵያ ሁለት ቅምጥ መንግሥቶችን ማቋቋምና የአፍሪቃን ቀንድ በቁጥጥር ሥር ማዋል ነበር:: ከዚያም "የፈዲሬሽኑ" ነገር::

ይሁንና፣ ከዚያ ጊዜ በኋላ፣ ሶማሊ "ከህደት ተፈጸመብኝ" በማለት በሃገሯ ውስጥ የሚገኘውን የሶቪየት ህብረት ተወካይ በ48 ሰዓት ውስጥ አባረረች:: ከፊዴል ካስትሮ መንግሥት ጋር የዲፕሎማሲ ግንኙነቷን አቋረጠች:: የምዕራብ አገሮች የፖለቲካ፣ የመሣሪያና የማተርያል እርዳታ እንዲሰጧት አካባቢዎችን ማበስ ጀመረች:: ኢትዮጵያችንም፣ የሩስያ ተስፋፊና ጣልቃ ገብ መንግሥት በእጅ አዙር የሚገዛት የቅኝ ገዛት ወደ መሆን አመራች:: በዚህም የሶማሊ ወረራና የሩስያ ተስፋፊዎች ሤራ የመጀመሪያው ዙር መጋረጃ ይዘጋል:: ከዚህ በኋላ የሆነው የታወቀ ነው::

ጠቅላላው የአፍሪቃ ቀንድ አካባቢ በከፍተኛ ደረጃ የሁለቱ ሃያል መንግሥታት የፍልሚያ አውደማ ሆነ:: የአካባቢው ህዝቦች ፣ ሁለቱ ሃያላን መንግሥታት ለሚያደርጉት ጦርነት ጥዳ ለመሆን ተጋለጡ:: ኢትዮጵያም ሆነች ሶማሊ በህዝቦቻቸውና በሃገራቸው የሚያዙ ነፃ ምድሮች መሆናቸው ቀርቶ፣ የሁለቱ ሃያላን መንግሥታት ዓለም አቀፋዊ ስትራቴጂ ውስጥ ወደ ተራ ጠጠርነት ተቀረፁ:: ሶማሊ ለአሜሪካ የጦር ሰፈሮች ሰጠች:: ቅምጡ ወታደራዊ አምባገነን መንግሥትም ኢትዮጵያን የሩስያ ተስፋፊዎች የጦር ሰፈር አደረጋት:: ዘመናዊ የጦር ሰፈሮችን /የዳህላክ ደሴቶች፣ ምፅዋ፣ አሰብ/ ለመስጠት ተዋዋለ:: በሁሉም በዓት፣ ዘመናዊ የባዕድ ወታደሮችን ለማስፈር እያስፈሰፈ ነው:: በካባቢው ያለው አደገኛ ሁኔታ የሚያመለክተው ሁለቱ ሃያላን መንግሥታት በአፍሪቃ ቀንድ ላይ የሚያደርጉትን ከባድ ጦርነት ነው:: የነርሱ ባልሆነው ጦርነት የሚረገፉት ደግሞ የአካባቢው ህዝቦች መሆናቸው የታወቀ ነው:: በዚህም፣ ብሄራዊ ነፃነታችንን አስረገጠ ኢትዮጵያን የሩስያ ተስፋፊዎች የእጅ አዙር ቅኝ ገዛት ኃስደረጋት ቅምጡ መንግሥት ከተጠያቂነት አያመልጥም:: ዛሬ "በርበራ ኪስማዮ ጦርነት ወረራ" እያለ የዓለም ህዝቦችን ማደንቆሩ ይህንን ሃቅ አይቀይረውም:: "ቀደምውንስ ኢትዮጵያን የሩስያ ጦር ሰፈር ባታደርጊት/ በኢትዮጵያ የሰፈሩትስ ሩስያዊያን ለየትኛው የሰላም ተልዕኮ ይሆን?" ሲሉ ነፃ ህዝቦችና ሃገሮች መሣለቂያ ቢያደርጉት ማየቱም አያሰደንቅም::

— <u>የሩስያ ተስፋፊ መንግሥት ሥር መስደድ</u>

እንደሚታወቀው፣ ከሰኔ/ሐምሌ 1969 ጀምሮ፣ ሃገራችን አይታው የማታውቀው አልቁ መሳፍርት የጦር መሣሪያ በአንቶኖቭ እየተጫነ ምድራችንን አጥለቀለቀው:: ይህች ያሸው ወረራ በፈጸመበት፣ የባዕድ ወታደሮችን "ዶረቡልኝ" ብላ የማታውቅ የኩሩ ጀግኖች አገር በጥቂት ባመንታት ውስጥ በሺህ በሚቆጠሩ በኩባና በደቡብ የመን ወታደሮች ጫማ ተረገጠች:: 30 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ጀግና ህዝብ ያንዲት ሶማሊን ጦር መቋቋም ያቃተው ይመስል፣ "የወዳጅ አገሮች" ጦር በምድሯ ላይ ፈሰሰ:: ህዝቧ እንኳን ከፍሎ ቆጥሮም ከማይጨርሰው ዕዳ ውስጥ ተዘፈቀ::ደርግ በሩስያ ተስፋፊዎች ኪስ ውስጥ የወደቀ ጠጠር ሆነ::



ከንግዲህ ያለው ታሪካችን፣ ሰሀዶ ገና በመጋቢት 1969 ዓ.ም. እንዳለው፣ በንዱ በኩል በአብዮቱ መኮላሸትና መቀልበስ ፣ በሌላው በኩል ደግሞ በብሄራዊ ነፃነታችን መገበስ፣ እየተጠናከረ በመጣው የሩስያ ተስፋፊና ጣልቃ ገብ መንግሥት ተፅዕኖና ቁጥጥር፣ በዘበዛና ምዝበራ አይነተኛ ሆነ:: ህዝባዊ ሃይሎች ተራ በተራ ተጠቁ:: ለሦሥት ዓመታት ሙሉ ለህዝባዊትና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የተዋደቀው ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ የሩስያ ተስፋፊዎች ቅምጥ—አሻንጉሊት በሆነ የወታደራዊ አምባገነን አገዛዝ ሥር ወደቀ::

ያ ያለአንዳች የውጭ ዕርዳ በሃቀኛ አገርና ወገን ወዳድ የኢትዮጵያ ተራማጆች የተዘጋጀው፣ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ በማጤን የሰፊውን የኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት መነሻ በማድረግ የወጣው፣ ያ የአብዮትን ሃይሎች ሁሉ ለመሰብሰብና በዲሞክራሲያዊ የህብረት መድረክ ላይ ለማሰለፍ ሆኖ የተዘጋጀው ሳይንሳዊው የአብዮታችን መመሪያ— የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራማችን ዕውነተኛ የሃገሪቱ የፖለቲካ መመሪያ መሆኑ ቀርቶ፣ የዘመናዊ ባንዳዎችና ተስፋፊዎች መመፃደቂያና ጭምብላቸው እንዲሆን ተበየነበት:: ያ ብሄራዊ ነፃነታችንን የማያስደፍርና የማንም ሃያል ሆነ የባዕድ መንግሥት የበላይነትን ተፅዕኖ የማይቀበለው፣ እንኳንስ እንደምዕራብ ኢምፔሪያሊዝም በገልፅ የሚጋፋንን ቀርቶ፣ እንደ ሩስያ ተስፋፊ መንግሥት "በሶሺያሊዝም"ና "በወዝአደራዊ አለም አቀፋዊነት" ተከልሎ ለሚመጣ ሃይልም መግቢያ ቀዳዳ የማይሰጠው፣ የኢትዮጵያን ህዝቦች ጥቅምና የራስ ዕድል በራስ የመወሰን መብት ማስቀደም እንጂ፣ አገራችን የማንም ሃያል መንግሥት ተቀጥላ መሆኗን አምርሮ የማይቀበለው የአብዮታችን ፕሮግራም ከተስፋፊዎች መግባት ጋር ተያይዞ አለቀለት::

የወዝአደራዊነትና የሶሺያሊዝም ሽታውም በማይነፍስበት "በሶሺያሊስት ወንድማማችነት" ና "በወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት" ስም አጊጦ የብሄራዊ ነፃነታችንን በር የሰረገደው የሩስያ ተስፋፊና ጣልቃ ገብ መንግሥት ምድራችንን ከረገጠ ወዲህ፣ የቅልበሳው ሴራ በየፈርጁ ተጠምጥሞ አብዮታችን ተቀለበሰ:: "እኔ አውቅላችኋለሁ" በሚል የገዢዎች ፈሊጥ የኢትዮጵያ ሃቀኛ ተራማጆችን፣ አገር ወዳዶችን፣ ዲሞክራቶችንና አርበኞችን ሁሉ ከጥቃቅን የዕለት ጉዳዮች አንስቶ እስከ ጠረፍ ገንበር ድረስ በየመስኩና በየሥፍራው ተፈታትና ቁጥጥሩንና ተፅዕኖውን አንሰራፉ:: የመላ ሃገሪቱን ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ ተቋሞችን በዕጁ እያስገባ ሄደ::

በቅድሚያ፣ በ"ጦር ዕርዳታ"ስም በመላው የኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ የበላይነትን ተቀዳጀ:: የኢትዮጵያን ሠራዊት ቢሻው በመሣሪያ ቢሻው በሎጂስቲክ፣ ቢሻው በጦር ትዕዛዝ፣ ቢሻው በአሥራት በዝውውርና በሞት ቅጣት ጭምር እንደልቡ ያወጣውና ያወርደው ጀመር:: የእዝ ሰንሰለቱን ያዘ:: እንደውነቱም ከሆነ፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት በታሪኩ ውስጥ እንደዚህ ጊዜ የባዕድ ጦር"አማካሪዎች"ና አዛዦች ተገዢና ተላላኪ ሆኖ አያውቅም:: የኢትዮጵያ ጦር አዛዦች እንደዚህም ዘመን ለስሙ የተቀመጡ አሻንጉሊቶች ሆነው አያውቁም:: በዚህ ላይ፣ ወደ 20 ሺህ የሚጠጋ "የወዳጅ" ጦር ከነጦር ሰፈሩ ተንሰራፍቷል:: እስከዚህ ድረስ የኢትዮጵያን ምድር የደፈረ የባዕድ ጦር ቢኖር የፋሺስቱ ሙሶሊኒ ጦር ብቻ ነበር::

## 3. <u>የሩስያ ተስፋፊ መንግሥት ወታደራዊ ተፅዕኖና ቁጥጥር</u>

በታሪክ ውስጥ መቼም ቢሆን እንደታየው፣ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ነፃነት ለመድፈር የሞከሩ የባዕድ ሃይሎች "ኢትዮጵያን ቅኝ ገዛት ልናደርግ ነው" ሲሉ ከማስጠንቀቂያ ጋር የመጡ የዋሆች አልነበሩም:: ባለፈው ከፍለዘመን ጣልያንም ሆነች ፈረንሳይና እንግሊዝ፣ በዚህ ከፍለ ዘመን ደግሞ እንግሊዝም ሆነች የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም፣ ማናቸውም ቢሆኑ ኢትዮጵያን የቀረቧት ዕጅ መንሻ በይዞ አልነበረም:: እንዳው ታሪክን እናስታውስና፣ ባለፈው ከፍለዘመን ኢትዮጵያን ለመቃረጥ ከቋመጡ መንግሥታት ጋር፣ የቀደምቷ ሩስያ ድርሻዋን ለማግኘት ስትሯሯጥ፣" ለኢትዮጵያ የክርስትና ሃይማኖት ጳጳስ የማቅረብ መብት ይገባናል" ስትል ነበር ብቅ ያለችው:: ታዲያ፣ ያኔ የተሳከው የጳጳሱ የሃይማኖትና የሳይንስ ምርምር ቡድን "ወታደራዊ እንጂ ሳይንሳዊና ሃይማኖታዊነት ምኑ ላይ ይሆን?" በመባል በጊዜው የታሪክ ፀሐፊዎች ማፌዣ ሆኖ ነበር:: የዘመኑ ዘርቻም፣ ብሄራዊ ነፃነታችንን የደፈረት "ኢትዮጵያን ልንገዛ መጣን::" የሚል መፈክር አንግበውልን እንዳልሆነ ግልፅ ነው:: ለኢትዮጵያ አገር—ወገን ወዳጆች እጅ እጅ ያ

ሰውን ያነኑ"የድጋፍ" መዝሙር ይዘው ነው::
በቅርጫ የሚቀርበው የዘመኑ የሩስያ ተስፋፊዎች የ"ድጋፍ" መፈክር
የጦር መሣሪያ "ዕርዳታ" ናው:ሰር ነው:: ኢትዮጵያንም በመሠረታዊ የቀረቧትም
ስጠትኢታቸው ስሆነው ስደርግ መንግሥት መሣሪያና የወታደራዊ "ድጋፍ" በመስ
ጠት ስም ነበር:: በዛሬ ሰዓት ሃገራችን ዛሬ በከፍተኛ ዕዳ ውስጥ ስትማስች::
ሃገራችን ዛሬ፣ በገመት ፻3.5 ቢሊዮን ዶለር የሩስያ ተስፋፊዎች ባለ ዕዳ ሁ
ናለች:: ይህ ስጦር መሣሪያ ብቻ የሚከፈለው ዕዳ ነው:: በተጨማሪ መሣሪያውን
ለማስማመድና ለጦር መኮር በሚል፣ ቀጥራቸው ያልታወቀ የሶቭየት ህብረትና የተቀጠ
ሳያቷ አገሮች የጦር "አማካሪዎች"በምድሪቷ ሳይ ፈሰዋል:: የኢትዮጵያን ሰራዊ
ት እዝ መስ ስመስ እየተቆጣጠሩ ናቸው:: በመጠረሻም፣ ከ20ሺህ የማያንስ የበ
ዕድ ጦር በምድራችን ላይ ሰፍሯል:: እንግዚህ ሁለት ወንጀሪ? የጦር ሠፈሮችን
በሁርጮ.አሰበ በማቋቋም ላይ ይገኛሉ:: የአሰበ ወደብንና የዳህላክ ደሴቶችን
እንደ ባህር የጦር ሰፈር ጠበያ አድርገው መቆጣጠር ከጀመሩ ሰንበተዋል:: የተ
ረፈ ሃገር ካሰንም ያበናል፣ ተጨማሪ የጦር ሰፈሮችን ለመስጠት፣ ሸለቃ መንግሥቱ
ሃይለ ማርያም ከጥቅምት 18ቀን እስከ ህዳር.3 1973 ደረስ ... ከረምሊን
ውስጥ ... ሲቀፍል ከርሞ መጥቷል:: ዳህላክ ደሴቶችና ቃፀ.ቀ ውስጥ ከባድ የሩ
ስያ ጦር ሰፈር፣ እንዲመሰረት ከመስማማቱ በስተ... ተጨማሪ የባዕድ ወታ
ደሮች በሃገራችን እንዲሰፍሩ ጠይቋል:: ይህ ሁሉ ደግሞ እንደሚታወቀው፣ የዘመኑ
በገዳዎች ከዘመኑ ገሮች ጋር ባደረጉት የዘመኑ ወጨሌ ውል ከሁለት ዓመት በፊት
የተረጋገጠ ነው:: በዚህ በህዳር 1 ቀን 1971 ዓ.ም. ቅምጡ መንግሥት በተ
ፈራረመው በዝነኛው የ20 ዓመት የባርነት ውል በሃገራችን ነፃነታችን መሮ በሙሉ
ለሩስያ ተስፋፊዎች ተሸጧል::
እነዚህ ... የታወቁ ናቸው:: በዝርዝር እንመለስባቸውም::
የሩስያ ተስፋፊ መንግሥት በሃገራችን ላይ የተቀዳረው ወታደራዊ ተፅዕኖና ቁ
ጥጥር ለማፀናት የሚፈጽማቸውንና የፈጸማቸውን ሌሎች በርካታ ገዳዮች ይልቀኑ
እንመልከት::
የሱማሌ ወረራ እንደተከፈተብን፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት መርጧና ግዴታ
ለሃገር ነፃነትና ክብር መቆሚያ ነበር:: ስለሆነም፣ ፈጥኖ ወደ ምሥራቅና ደ
ቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ አቅጣጫ ዘመተ ነበር:: ለድሃይው ቢሮክራሲ ስንት አሸጥር
ር በፈጸመበትም፣ ወራሪውን የሱማሌ ጦር ገነባረን ባያጥፍ ፊት ለፊት ተጋጥሞ
ተቋቁሟል:: ነገር ግን ጥያት የወረደበት በሱማሌ ጦር ብቻ አልነበረም:: በ
አድሃሪው የሲቪል / ሚሊተሪ ቢሮክራሲ ብቻም አልነበረም : በተጨማሪ፣ የከሃዲ
ው የኛ አስታ ለገሰ አስፋው ቡድን፣ ይህ ነው የማይበል የጥፋትና የፍጅት ጠ
ርነት ከበስተጀርባው ከፍቶበታል:: በዚህ ወቅት ውስጥ፣ አያሌ አብዮታዊያንና
አገር ወዳድ መኮንኖች፣ ወታደሮችና የዘማች ሠራዊት አባሎች "ቆኘ መንገደኛ፣
ጠበበ ብሄርተኛ፣ ሠርጐ ገብ ..." እየተባሉ እንደተጨፈጨፉ፣ ለአሥር ስቃይ
እንደተዳረጉና እነበም ቢባል በጡረታና በዝወውር ስም እንደተገለሉ አገር ያው
ቀዋል:: ይህ በኢትዮጵያ ሰራዊት ላይ ከበስተጀርባው የተፈጸመው ጥያት፣ የሩ
ስያ ተስፋፊዎች ሠራዊቱን እንደልባቸው ለመቆጣጠር እንዲችሉ በማለት የወሰዱት
/ያልወሰዱት/ እርምጃ ነበር:: ዛሬም እንደቀጠለ ነው:: የተስፋፊዎች ወታደ
ራዊ ተፅዕኖና ቁጥጥር አንደኛው ዘዴ፣ ሠራዊቱን የነሱ ወታደሮች አልባ አድር
ጉ ማስቀረት እንደሆነም በዚሁ እንረዳለን:: የሚፈልጉት በእነርሱና በእና መ
ካከል የቅኝ ገዢዎችና የተገዢዎች ግንኙነት እንዲኖር ነው:: እነርሱ ጌቶች
እና ሎሌዎች::
ሁለተኛ፣ በወታደራዊ ቴክኒክም ረገን፣ የሩስያ ተስፋፊዎች የኢትዮ
ጵያ ሠራዊት የሰለጠኑ የወታደር ቴክኒሽያኖች እንዲኖረው አይፈልጉም:: በዚህ
አንፃር በየጦር ክፍሉ የሚፈጸመው ደባና ተንኮልም እጅግ ብዙ ነው:: ለምሳሌ
ም ያህል፣ የሩስያ ቴክኒሽያኖች መሣሪያዎችን በሚገጣጥሙበት ወይንም በሚያድሱ
በት ወቅት፣ የኢትዮጵያ ወታደራዊ ቴክኒሽያኖች እንዳይጠጋቸው በጥብቅ የተከለ
ከለ ነው:: ሊሰው ዋርቶ በገዛ ሃገራችን የገዛ ቴክኒሽያኖቻችንን እንኳን ለ
ማሰልጠን የተከለከልን ይመስላል:: አንድ ምሳሌ እንመልከት::
በአንድ ወቅት በ1972 ዓ.ም. ውስጥ የመገናኛ መሣሪያ ለመግዛት
ይፈለገና፣ በርካሽ የሚገኝበት አከባቢ ይታሰባል:: በዚህም መሰረት፣ የሩስያ
ተስፋፊዎች ከሚያቀርቡት ማሣሪያ ጋር ሲመጣጠን ከጥራቱ ሊላ፣ በቀጋውም
እነስተኛ የሆነ የመገናኛ መሣሪያ ከአሜሪካው አይ ቲ ቲ ኩባንያ ይገኛል::



ይህ መሣሪያ እንዳይገዛ ተስፋፊዎቹ በተለመደው አይን ያወጣ መንገድ ከፍተኛ ተፅ
ዕኖ ያደርጋሉ:: ይሁንናም፣ ጉዳዩ የሚመለከተው ባለሥልጣን፣ መቼም ኢትዮጵያዊ
ነውና ድንገት ብሄራዊ ወኔው ተነስቶበት ይመስላል፣ በርካሽ ከተገኘበት ይገዛ
በሉ በድፍረት ያዛል:: በአይ ቲ ቲ ይገዛል:: ይህ መሆኑን የሰሙት የራሽያ
ነጋዴዎች ያዙን ልቀቁን ይላሉ:: በዚህ ፍራቻ፣ የአይ ቲ ቲው የመገናኛ መሣ
ሪያ 'አልተገዛም" ተብለው ይሸኛሉ:: ይህ መሣሪያም መገዛቱን እንዳያውቁ ታስበ
የመሣሪያውን አሠራር ለማስተማር የመጡ አሜሪካኖች ከራሽያኖቹ ጋር እንዳይገናኙ
ጥንቃቄ ይደረጋል:: ለዚህ ታስበ የኢትዮጵያ ቴክኒሽያኖች በድብቅ እንዲሰለጥኑ
ይደረጋሉ:: በሸሸገም ረገን፣ እ... ላይ የኢትዮጵያ ቴክኒሽያኖቻችን የሚያሰለ
ጥኑ መገኘታቸውን ማስታወስ ያስፈልጋል:: የተስፋፊዎቹ "አቀፊዎች" ግን እንዲ
ን ሊያሰለጥኑ ቀርቶ፣ የአንድ መሣሪያ ተራ ማንቀሎችን /በኢትዮጵያዊያን ዕጅ
እንዳይወድቁ/ ተንተርሰው ማደር ነው የሚቀራቸው:: ይህን የመሰሉ በኢትዮጵያ
አየር መንገድ የደረሱ ብዙ ተመባበይ 'አስደናቂ' ነገሮች አሉ:: እንተወው::
እንደውነቱ ከሆነ ግን፣ ዓለም ዛሬ ከደረሰችበት የባህል እድገት አንፃር ስን
መለከተው፣ ይህ በ18ኛው ክፍለ ዘመን የቀረ፣ እንኳን ለጠለቶቻቸው ለወዳጆቻ
ቸውም እጅግ አባፋሪ የሆነ በህሳዊ ኋላ ቀርነት ና ዘረኝነት ነው ማለት እን
ገደዳለን:: እያ: የሚፈለገው በእኛና በነርሱ መሃከል የቅኝ ገዢዎችና ተገዢ
ዎች ግንኙነት እንዲኖር ነው:: መናልባትም ፊውዳል ፊውዳል የሚሸት:: እነርሱ
ጌቶች እና ሎሌዎች::
ሲሰም ደግሞ፣ "ስትምህርት" እየተባለ ወደ ሶቭየት ህብረት የተወ
ሰዱት ቴክኒሽያኖችና ጋይለቶች ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ሃገራቸው ሲመለሱ፣
እነርሱ እጅግም ያላወቁበትን ሚግ የኢትዮጵያ ጋይለቶች እንደማይሆን አድርገው
ሲያበሩሳቸውና ለኢትዮጵያ አሉሚ እንደማቡጁ አድርገው የና ቴክኒሽያኖች፣እነርሱ በ
ዕዳ የበጡንን መሣሪያዎችና አይሮፕላኖችን ሲያሸሹ፣ ማስታወሸ የወሰዱብትን ደ
ብተርና መዝገብ ሁሉ እንዳያስረክቡ ሲደረጉ ምን ይበላል?? ነገሩ ያው የጌታ
ና የሎሌ ጉዳይ ነው:: ይህ ሁሉ ሲያንባቸው፣ በስንት ውድ ዋጋ የመጡት አይ
ሮፕላን ሞተሮች ሲበላሹ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲታደሱ እንኳን አይፈቀድም:: ሞ
ተሮቹ እንዳሉ ወልቀው እንደገና በስንት ወጪ ወደ መስኮብ ተልከውና እዚያው ታ
ድሰው ይመለሳሉ:: ምን አለፋን፣ የሩስያ ተስፋፊዎች ወታደራዊ ተፅዕኖና ቁጥ
ጥር ሁለተኛው ዘዴ፣ ሠራዊታችንን የወታደራዊ ቴክኒሽያኖች አልባ አድርጉ ማስ
ቀረት እንደሆነምበዚሁ እንረዳለን:: የሚፈለገው የቅኝ ገዢና ተገዢ ግንኙነት
ነው:: ያው ፊውዳል ፊውዳል የሚሸተው:: እነርሱ ጌቶች እና ሎሌዎች::
ሦስተኛው ዘዴ፣ ሃገራችንና ህዝቦቿን ከማያልቅ ጦርነት ውስጥ በመ
ከተት በሚፈጸመው ሤራ የሚካናወን ነው::የሩስያ ተስፋፊ መንግሥት በሃገራችን
የውስጥ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ፣ በምድሪቷ ላይ ከሰሜን እስ
ከ ደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ በየጊዜው እየሰፉና እየተወሳሰቡ የሚካሄዱ
ት ጦርነቶች ለዚሁ መስክር ናቸው:. የሩስያ ተስፋፊ መንግሥት፣ "የኢትዮጵያ
ብሄረሰቦች አንድነት በመፈቃቀድና ስእኩልነት፣ እርስ በርስ በመረዳዳትና በወ
ንድማማችነት ላይ ተመሥርቶ" ሃገሪቱ ስሰምናጥንካረን ከምታገኝ ይልቅ፣ በወን
ድማማች ጦርነት ተወጥራ ብትዳከም ይመርጣል:: በዚህ ሤራው የሚፈስስትም ጥቅ
ም ሰብቻው ነው:: በአንድ የጦር ክፍል ብቻ የሚደርሰውን ወስደን፣ ይህን ጉዳ
በአሃዝ እየደገፍን ማሳየት አለብን::
ከፍ ብለን እንዳልነው፣ ኢትዮጵያ እንኳን ከፍለ ቀጥራም የማትጨር
ሰው የተስፋፊዎች ዕዳ ውስጥ ተዘፍቃለች:: ይህ ዕዳ የጦር መሣሪያ እንዲ የ
ልማት እንዳልሆነ ደግሞ የታወቀ ነው:: ታዳያ የገዛ ህዝቦቿንም አልቀው፣ ኢ
ትዮጵያም በገፍ እየተበዘበዘች እንዴት እንዴት ተደርጋ ባለዕዳ እንደሆነች ማ
የቱ አስፈላጊ ነው:: ባንድ በኩል፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች እንደቅጠል እየረገፉ፣
በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ በሬ ህዝብ ደረቅ ሽር እርበት በችጋር፣ በረሃ
ብና በችነፈር እያለቀ እንዴት ባንተም እንኳን በከንቱ "ስትባበሉን" ማየቱ አ
ገር—ወገን አፍቃሪን ሁሉ ያንገበግበል:: "የሚያበኩትኝ" ግን ባንተሞች አይደሉ
ም:: ሚሊዮኖች ናቸው:: ምሳሌዎቹ በአየር ሃይል ብቻ የደረሱና የሚደርሱ ና
ቸው::

በሚግ አይሮፕላን ዋጋ እንጀምርና፣ ተስፋፊዎች"በሶሽያሊስት ወንድ
ማማችነት" መሣሪያ ለመሸጥ ውለታ ሲገቡ፣ ግማሽ ዋጋ ብቻ እናስከፍላለን በዋች
ናቸው:: ይሁንና፣ የኋላ ኋላ ተተምኖ ሲመጣ ለአያንዳንዱ ዕቃ የሚከፈለውአጥፍ

ን ይዛል:: ያለ ብዙ ሂሣብ፣ ለምባሌ 4 ሚሊዮን የሚያወጣው ሚግ አይሮፕላ
ን 8 ሚሊዮን ይከፈልበታል:: ለ8 ሚጎቻችን 4×8= 32 ሚሊዮኖች ተጨማሪ
ተከፍሎባቸዋል ማለት ነው::

ይህ 8 ሚሊዮን የሚያወጣው አይሮፕላንና በዚህ የሚካሄደው ጦርነት
የሚጠይቀውን ወጪ እንመልከት::-

1. አንዱን ሚግ አንድ ጊዜ ብቻ ለማብረር 15 000 የአሜሪካን
ብር ይጠይቃል::

2. ውድ የሆነው የአይሮፕላኑ ትጥቅ፣ ለአንድ ሮኬት 200 የአሜሪካ
ን ብር፣ ለአንድ ጥይት 20 የአሜሪካን ብር፣ ለአንድ ቦምብ 3000 የአሜሪካ
ን ብር ይፈጃል:: በጠቅላላው አንድ ሚግ አጥቅቶ እንዲመለስ ለማድረግ 45000
የአሜሪካን ብር ወጪ ይደረጋል:: የሚሰማሩት ሄሊኮፕተሮች የሆኑ እንደሆነ ደግ
ሞ 35000 የአሜሪካን ብር ይጠይቃል::

3. በጦርነት ላይ በአማካኝ የወጣ ወጪን እንመልከት:-

ሀ/ ኤርትራ:-

በቀን የሚደረግ አማካኝ የሚግ በረራ — 85
ለአንድ ጊዜ በረራ ወጪ — 45000 የአሜሪካን ብር
የቀኑ ወጪ — 3825000 የአሜሪካን ብር

ቅምጡ መንግሥት በኤርትራ ውስጥ የትምክህተኛ ጦርነትን ሲያፋፍም፣
በቀን 85 የሚግ በረራዎች ለ60 ቀናት በተከታታይ ያካሄዳል::

ለ60 ቀናት፣ 60× 3825000 = 229.500.000 /229 ተ
ኩል ሚሊዮኖች/ የአሜሪካን ብር ወጪ ይደረጋል::

ለ/ ትግራይ:-

በቀን የሚደረግ አማካኝ የሄሊኮፕተር በረራ — 15 /15 ሄሊኮፕ
ተሮች ይሰማራሉ ማለት ነው/
ለአንድ ጊዜ በረራ ወጪ — 35000 የአሜሪካን ብር
የቀኑ ወጪ — 525000 የአሜሪካን ብር

ቅምጡ ወታደራዊ መንግሥት የትምክህተኛ ጦርነትን በትግራይ ሲያፋፍም
በአማካኝ ለ60 ቀናት በተከታታይ ቢያንስ በየቀኑ 15 ሄሊኮፕተሮችን ያሰማራል::
ይህም፣ 60× 525000 = 31.500.000 /31 ተኩል ሚሊዮኖች/ የአሜሪ
ካን ብር ወጪ ያስከትላል::

ወጪዎቹን በሙሉ ባንተምን በአሜሪካን ብር እንዳሉ የተውናቸው ለሩ
ስያ ተስፋፊዎችም የምንከፍላቸው በአሜሪካን ብር /በውጭ ምንዛሪ/ ስለሆነ ነው::
ይህ ሁሉ ወጪ እንግዲህ፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች በሚወርዱባቸው በምብና ጥይት እያ
ለቁ በረሃብና ችጋር እየተጠበሱ፣ በቅምጡ መንግሥትና በሩስያ ተስፋፊዎች ጦርነ
ት ሳቢያ፣ ኢትዮጵያ በውጭ ምንዛሪዋ ለተስፋፊዎች በከፊል አሁኑኑ የምትከፍለው
ሲሆን፣ በከፊል ደግሞ የተስፋፊዎች የሂሳብ መዝገብ ውስጥ፣ የኢትዮጵያ የዕዳ
መዝገብ ውስጥ የሚሰፍር ነው::

በአራትም ማዕዘን የሚካሄደውን ጦርነት ሲጠቀልል፣ በሌሎች የጦር ክ
ፍሎች የሚደረገውን ወጪ ሲጨመር፣ ጠቅላላ የጦርነቱ ወጪ ምን ያህል እንደሚሆን
አንባቢ መገመት አያቅተውም:: እና ግን እዚሁ አየር ሃይል እንቆይና እንቀጥል::

ከፍ ብለን እንዳልነው፣ እነርሱ ጌቶች እና ሎሌዎች እንዱንሆን ነውና
የሩስያ ተስፋፊዎች የእኛ ቴክኒሽያኖችን የእነርሱ ሚጎች አጠገብ ዘር እንዳሉ
አይፈቅዱላቸውም:: በመሆኑም የአንዱ ሚግ ሞተር ብልሽት ሲደርስበት ሞስኮ ሄዶ
ካልተጠገነ አይሆንም:: የ35 ዓመት ልምድ ያለው የአየር ሃይል የመይንተናንስ
ክፍል ይህን ለመጠገን ምናልባት "ቢፈቀድለት" ከ5000 ብር የበለጠ አይፈጅበ
ትም ነበር:: "ሮዓጀቻችን" የሚጠይቁን ግን የ5000 መቶ ጊዜ እጥፍ የሆነው
ን ግማሽ ሚሊዮን የአሜሪካን ብር ነው::

ይህንኑ ጥገና በሚመለከት ደግሞ፣ ምናልባት ጥገናውን በሃገራችን
ለማድረግ ይፈቀድልን ዘንድ፣ ለከባድ ጥገና ምን ያህል የሰው ሃይል እንደሚያ
ስፈልግ በኢትዮጵያዊያንና በሩስያዊያን አዋቂዎች ጥናት ተደርጎ ነበር:: ኢትዮ
ጵያዊያኑ ባደረጉት ጥናት 700 የቴክኒክ አዋቂዎች ብቻ እንደሚያስፈልግ ሲደር
ሱበት፣ የተስፋፊዎቹ የጥናት ውጤት ደግሞ 25000 ሰዎች እንደሚያስፈልጉ ያመ
ለክታል:: ምክንያቱ ግልፅ ነው:: ጥገናው በሃገራችን እንዳይካሄድ፣ እነርሱም
ከተራበው የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ መንጋጋ ግማሽ ግማሽ ሚሊዮን የአሜሪካን ብሩ
ቻውን እየነጠቁ ለመቀየት፣ እናም የብሄራዊ ውርደት ሸማችንን ተከናንበን እነርሱ
ን እጅ እየነሳን እንድንኖር ነው:: ያው ፊውዳል ፊውዳል የሚሸት የቅኝ ገዢና
ተገዢ ግንኙነት:: እያ : እነርሱ ጌቶች እና ሎሌዎች::

በመጨረሻም፣ የሩስያ ተስፋፊዎች አይን ያወጣ ዝርፊያ ያካሄዱበትን
አንድ ምሳሌ አውስተን እናብቃ:: የሚጋዝ አይሮፕላንን የሚመለከት ነው::
ተስፋፊዎቹ በገቡ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታት፣ በአየር ሃይል ውስጥ የነበሩን
የሚጋዝ አይሮፕላኖች መከራየት ግዴታ ነበር:: ለአንድ ጊዜ በረራ 10.000
የአሜሪካን ብር ይከፈላል:: በወቅቱ እስከ አራት ጊዜ ደርቦ መልስ በረራ ይ
ከናወን ነበር:: ይህም ሁለት ዓመት ማለትም፣ 730 ቀናት ሙሉ ነበር:: በ
ትንሹ በቀን በአማካይ ሁለት በረራዎች እንኳን ተደርገዋል ብንል፣ የነዳጅና የ
በውሃይል ወጪን ሳይጨምር በጠቅላላው 15 ሚሊዮን የአሜሪካን ብር ተዘርፈን
ነበር ማለት ይቻላል:: ይህም እንደተለመደው ያው በአሜሪካን ብር /በውጭ
ምንዛሪ/ በቀጥታ ወደ ተስፋፊዎቹ ባንክ ይተላለፍ ነበር:: በመጨረሻም የኪራዩ
ገንዘብ እንዳይበዛብን አስበውልን ይመስል፣ የሚጋዝ አይሮፕላን ከነርሱ እንድ
ንገዛ እንሆናለን:: አሥር ይገዛሉ:: ዋጋቸው እያንዳንዱ 10 ሚሊዮን፣ መቶ
ሚሊዮን የአሜሪካን ብር ነው:: የአገልግሎት ዘመናቸው አምስት ዓመት ብቻ ነው::
እነዚህም ከግማ እቅም እንኳን ሲያልቅባቸው በሰዓቱ ተተኪ ስለማይላኩላቸው፣
አሥመራ ቆመው ከሚውሉት የነበሩን እንዲከራይ እንገደዳለን:: ታዲያ፣ እነዚህ
አይሮፕላኖች ከመግዛታቸው በፊት፣ በማንኛውም የአፈር ሜዳ ላይ ሊያርፉ የሚችሉ፣
ለመነሳትና ለማረፍ አጭር ሜዳ የሚበቃቸው፣ የአገልግሎታቸው ዘመን ቢያንስ አሥ
ር ዓመት የሆኑ፣ ከሁሉም በላይ ዋጋቸው ደግሞ እያንዳንዳቸው በስት ሚሊዮን የ
አሜሪካን ብር የሆኑ የሚጋዝ አይሮፕላኖችን ከካናዳ ለመግዛት እንደሚቻል የጉ
ዳዩ አዋቂዎች ሃሣብ አቅርበው ነበር:: አልተገዙም:: "በደም የተባበረው" የ
ዘመኑ ባንዳቆችና የዘመኑ ዘሮች ወዳጅነት መቅደም ነው:: "ቢገዙ ኖሮ" እን
በልና፣ እነዚህ ቢገዙ ኖሮ፣ ያ ለ"ደሚ መፍትሄ" 70 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር
ያስፈልገው ነበር ለተባለው ለተራበው የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ 70 ሚሊዮን የአሜ
ሪካን ብር በተረፈው ነበር:: ደግሞስ 70 ሚሊዮን ማን ይበጣል? በእርግጠኝነ
ት ለመናገር፣ የሩስያ ተስፋፊዎች እንደማይበጡ እናውቃለን:: እነርሱ "በወዳጅ
ነት" ኮሚቴዎቻቸው አማካይነት ለቻ አለቃ ለገቡ የተከለሱ መፅሀፍቶቻቸውን ከበ
ጡ፣ ለኮሚሽነር ይዱነቃቸው የስፖርት ጧማዎች ካበረከቱና በብዓዊነት ሲያምራቸው
ደግሞ ጥቂት ቶን የመድሃኒት ካርቶኖች ለኮሚሽነር ሽመልስ ከለገሱ መች አነባቸ
ው:: ሆኖም ግን፣ የቪስቃ መንግሥትን ተረት ለማስታወስ እዚህ ላይ እናም "እ
ፍኝ ቆሎ ይዘህ ከአሽር ተጠጋ" ይሉሃል ይሄ ነው እንላለን:: እና "ፍከቴያም
ችን"//የተከበረት' ቪስቃ ቢሞኙን ለተያዋ ሃይሉች ያወጡት ስም፡-"የደሃ ል
ጅ"አይቪልም?፡ ሎና 'ፍከቴያምችን' ግሚያንገበገበን እንግዲህ ይሸው የኢትዮጵያ
ህዝብ ችግር፣ የተስፋፊዎች ዘረፋና የቅምጦች ቅጥፕነትም ኑው:: የሩስያ ተስፋ
ፊዎችን የዘረፋ ታሪክ ተባስበን እንዘልቀውም::

እንግዲህ ተስፋፊዎችና ቅምጡ መንግሥታቸው በሰማዊ መፍትሄ እንዲያ
ገኙ በማይፈልጉት፣ በአራትም ማዕዘን በኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ላይ በሚደረገው
ጦርነት ሳቢያ ኢትዮጵያ ተወጥራ ብትዳከም፣ ተስፋፊዎች የማይመርጡበት ምንም ም
ክንያት እንደሌለ በትንሹ ከላይ ለማሳየት የሞከርነው ግልጽ ያደርገዋል ብለን
እናምናለን::

የሩስያ ተስፋፊዎች መንግሥት ባንድ በኩል፣ የመሣሪያዎች አቀባይ ሆ
ኖ ለተራዘመ ጊዜ ይቆያል:: ይህም በሌላ አነጋገር፣ የዘሬዎችን የሃገሪቱን
መሬዎች እንደዚሁ ለተራዘመ ጊዜ ጥገኖቹ ታዛዦች አድርጎ ይቆያል ማለት ነው::
በሌላው በኩል፣ የመሣሪያ ሸቀጡን ያለማቋረጥ በሃገራችን ላይ በማራገፍ ከፍተኛ
የገቢ ምንጮችን ያገኛል:: ሃገሪቱ ሊዕለት ዕለት እየጨመረ በሚሄደው ወታደራዊ
ዕዳ ውስጥ የበለጠውን ትዘፈቃለች:: ጠቅላላው ኢኮኖሚዋም፣ በዚያው መጠን የሩ
ስያ ኢኮኖሚ አገልጋይና ደጋፊ ሆኖ የበለጠውን ይታሠራል:: ጥገኝነታችን የተሟ
ላ ይሆናል ማለት ነው:: በዚሁ አንፃር፣ ሌላው ቀርቶ ለወታደራዊ አፕሬሽን ለ
ሚያደርጉት "ጥናቶች" የምንገፈግፈው ገንዘብ እንኳን በቀላሉ የሚገመት አይደለ
ም:: ባንድ በሆነ አካባቢ ወታደራዊ አፕሬሽን ሲታቀድ፣ ስለአካባቢው የአየርና
የጂኦግራፊ ባህሪይ፣ ስለህዝቡ ሁኔታና የሎጂስቲክ ጥያቄዎች ..ወዘተ. በቅድሚ
ያ ጥናቱ ይደረግ ይባልና ተያይዞ ዋጋው ይቀርባል:: ውጤት ይስጥ አይስጥ ጠያ
ቂ የለም:: ዋጋው ግን በዕዳ ይመዘገባል::ከዚህ በተያያዘ፣ ከመለዮ ለባሹ አ
ካባቢ እንደሚነገረው፣ የጦር እንቅስቃሴና እርምጃ ጥናቶችን /ወታደራዊ ምስጢሮ
ችን/ የሩስያ ተስፋፊ መንግሥት ለተቃራኒ ወገን አሳልፎ እንደሚሸጥ .ወዘተ ሁሉ
ይታወቃል::

በመጨረሻም፣ ይህ ሁሉ የማይሠራ ሆኖ ቢገኝ፣ የሩስያ ተስፋፊ መንግሥት ሃገራችንን በወታደራዊ ወረራ ለመያዝ የተጠናና በተገባር የተፈተሸ ዕቅዱ አለው:: የኢትዮጵያ ህዝብ አምጾ ቢነሳ፣ ልክ በአፍጋኒስታኑ ላይ እንደፈጸመው ሃገራችንን በጦር ለመውረር የሚያስችለውን ወታደራዊ አርምጃ በመዶራችን ላይ ፈትሾ አበቅቷል::ከአንድ አመት በፊት /ጥቅምት 1972/ ሁለት ብርጌድ የሩስያ ጦሮች /10 ሺህ የተሟላ መሣሪያና ስንቅ የታጠቀ ሠራዊት/ አንተኖቭ 22 በሚባሉ የጦር ማመላለሻ አውሮፕላኖች ተጭነው ከየመን ሩስያ በመነሳት፣ በቱርክና በኢራን ጠረፍ አድርገው፣ በሪያና ኢራክ ላይ ነዳጅ ከሞሉ በኋላ፣ ደቡብ የመንና ኢትዮጵያ መሬት ላይ አርፈው ወታደራዊ ልምምድ አድርገዋል:: ይህ ሁሉ ሲሆን፣ ቅጥሙ መንግሥት የሚያውቀው ኅንኛው ነገር አልነበረም:: ያም ሆነ ይህ፣ የሩስያ ተስፋፊዎች ገን ወታደራዊ አስፈላጊ ሲሆን፣ በ36 ሰዓት ውስጥ ለፈጸሙት እንደሚችሉ ፈትሸዋል:: የሸለሳ መንግሥት የዘገዶር ጉዞ ወጪት ቢታይ ደግሞ እስከነአካቴው በበዙ ሺህ የሚቆጠሩ ቁጠማሪ የሩስያ ወታደሮች በኢትዮጵያ መሬት ላይ ይበፍራሉ:: ያኔ ሃገራችን ከዛሬው የአፍሪቃ አፍጋኒስታን ሆነች ማለት ነው:: የኢትዮጵያ ሠራዊት ለሃገሩ ለወገኑና ለአብዮቱ ያልተቆረቆረ ይመስል፣ በገዛ አገሩ በገዛ መሬቱ በሩሽያ አዛዦችና በኩባ ወታደሮች እንደከብት እየተነዳና እየተረገጠ የገዛ ወገኑን እስከአሁን እንዳፈጀ መደረጉ ራሱ ኢትዮጵያን ቢያበፍር የሚናር ነው:: ከእንግዲህ ደግሞ፣ ይበስ ተብሎ በገዛ ሃገሩና በገዛ መሬቱ በይታመን ቁርቶ፣ በወገኑ ላይ ሺህ በሺህ የሚቆጠር ቁጠማሪ የበዕድ ጦር ከፈነ ጠበቶና ከዘዘበት፣ ኢትዮጵያዊውን ወታደር በኋራዊ ስሜት ምን ያዘው ይሆን ብሎ ከመጠየቅ በቀር የምንጨምርበት የለንም::

እንግዲህ በጭሩ፣ የሩስያ ተስፋፊ መንግሥት ወታደራዊ ተፅዕኖና ቀጥተር አስፈላጊ ሲሆን እስከወረራ ድረስ የታቀደ እንደሆነ መረዳት ቀላል ነው:: ኢትዮጵያን ሁለተኛዋ አፍጋኒስታን ለማድረግ አይናቸውን እንደማያሹ መረዳት ቀላል ነው:: የኢትዮጵያ ሃቀኛ ተራማጆች ዲሞክራቶች፣ አገር—ወገን ወዳዶችና አርበኞች ተገበር፣ ይልቁን ይህንን ውስብስብ ሁኔታ ተረድቶ ይህች ብሄራዊ ክብሯንና ነፃነቷን ጠብቃ የኖረች አገር የታሪክ በታቅን መልስ እንድታገኝ ለማይቀረው ትንንቅ ከዛሬው መተባበር፣ መዘጋጀትና መነሳት ነው::

* * *

ክፍል ሁለት ይቀጥላል

# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ
(ወዛደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር፣)
መብትና ጥቅም
የሚታገል ጋዜጣ

ቁጥር 74*

ታህሣሥ 29 1973

## ብሄራዊ ነፃነት ቢደፈር //

ይዘት

ገጽ

1. መግቢያ
   ሀ/ ለብሄራዊ ነፃነትና ለህዝባዊ አርነት የተደረገ ትግል .... 2
   ለ/ አዲሱ ፀረ ብሄራዊ ነፃነትና ፀረ ህዝብ ሃይል ......... 3
2. የሩስያ ተስፋፊ መንግሥት ወደ ሃገራችን መግባት
   ሀ/ ከየካቲት በፊት ..........................
   ለ/ ከየካቲት ወዲህ .......................... 4
   — ሶቭየት ህብረትና የሶማሌ ወረራ .............. 5
   — የሩስያ ተስፋፊ መንግሥት በሃገራችን ስር መስደድ .... 5
   .8
3. የሩስያ ተስፋፊ መንግሥት ወታደራዊ ተፅዕኖና ቁጥጥር ....... 9
4. የሶቭየት ህብረትና የአጋሮቿ የኢኮኖሚ ቁጥጥርና ዘረፋ ...... 15
   ሀ/ የጠራ ዕርዳታ ......................... 15
   ለ/ የኢኮኖሚው ግንኙነትና ቁጥጥር .................. 16
5. በሃገሪቱ የውስጥና የውጭ ፖለቲካ ላይ የሶቭየት ህብረት ቁጥጥር.. 20
   ሀ/ የሩስያ ተስፋፊዎች መግባትና የአብዮታችን መቀልበስ ...... 20
   ለ/ የተሟላ የፖለቲካ ቁጥጥር ......................... 21
6. ማህበራዊና ባህላዊ ተፅዕኖ .......................... 23
7. አቋማችን አንደገና
   1. ብሄራዊ ነፃነት ..........................
   2. የብሄረሰብ ጥያቄና የእርስበርሱ ጦርነት ............. 24
   3. ፍትህ፣ ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብት .............. 25
   4. የዘቀጠና የደቀቀ የኑሮ ሁኔታ፣ ረሃብና ችግር ......... 26
   5. የትግል አንድነት ጥሪ .......................... 26
   27

---

* ይህን ቁጥር ለዕትምና ለስርጭት ስንል ለሁለት ከፍለን አውጥተነዋል:: የመጀ



ክፍል ሁለት

### 4. የሶቭየት ህብረትና የአጋሮቿ የኢኮኖሚ ቁጥጥርና ዘረፋ

የሩስያ ተስፋፊ መንግሥት፣ በሌሎችም አገሮች ተለማምዶ የተካነበት፣ አንድን ነፃ አገር ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር የሚያደርግበት የተፈተነ ዘዴ አለው:: ይህም፣ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዳየነው፣ ባለ በሌለ ደባና ሤራ "በዓለም አቀፋዊነት.. በወዛአደራዊነት .. በሶሻሊዝም ..በወንድማማችነት ..በወዘተ" ስም በመጀመሪያ በተቻለ መጠን የነፃይቷ ወይንም የከጀላት ሃገር ብቸኛ የጦር መሣሪያ አቀባይ መሆንና የመከላከያ ሃይልን ሙሉ ለሙሉ በቁጥጥር ሥር ማድረግ ነው:: የነፃይቷን ወይንም የከጀላትን አገር ብሄራዊ ነፃነት ደፍር የመከላከያ ሃይሏን ቁጥጥሩ ሥር ከአደረገ በመሣሪያ ዕዳ ዕጅ ዕግሯን አውተብትቦ ኢኮኖሚዋን በቁጥጥሩ ሥር እንዲታደርገ ማስገደድ ነው:: አስቸጋሪም አይደለም:: ኢትዮጵያም ጥሩ መባሌ ሁናለች:: ከዚያ፣ 'የዕርዳታ ስምምነቶች፣ የኢኮኖሚ ውሎች፣ የንግድ ልውውጥ ስምምነቶች፣ "የስጦታ" አገልግሎት ድርጅቶች ...ወዘተ. የሚባሉ በርካታ የዘረፋና የጥገኛ ማድረጊያ ዘዴዎች ተያይዘው ይመጣሉ:: በዚህ ደረጃ የሚካናወኑት ጉዳዮች ሁሉ በሸው ስም በፈጸሙ የመጨረሻ ግባቸው አንድን አገር ሙሉ በሙሉ የኢኮኖሚ ጥገኛ፣ ብሎም የፖለቲካ ተገዢ ለማድረግ እንጂ ሌላ በጎ ዓላማ የላቸውም::

በኢኮኖሚው መስክ የሚካናወነው ቁጥጥርና ዘረፋ የሚጀምረው በገፍ ለገባውና ለሚገባው የጦር መሣሪያ ከምንከፍለው የጦር ዕዳ ክፍያ ስለሆነ ይህን በቅድሚያ እንመልከት::

#### ሀ/ የጠራ "ዕርዳታ"

ሶቭየት ህብረት ከሌሎች ከሌሎች "ዕርዳታዎች ሁሉ የሚቀላትና የሚ ትፈልገውም በመጀመሪያ የጦር "ዕርዳታ" የሚባለውን ማድረጉ ነው:: ምክንያቶቹም አጭርና ግልጽ ናቸው:: አንደና፣ የሶቭየት ህብረት የጦር ከምችት መጠንና ገደብ አጥቶ ተትረፍርፏል:: ሁለተና፣ እንደጦር "ዕርዳታ" አገሮችን በኢኮኖሚ ጥገኝነት ለመያዝ የሚያመቻች ዕርዳታ የለም:: ሶስተና፣ የሩስያ ተስፋፊዎች እንደ ኢትዮጵያ ላሉ አገሮች ከጦር መሣሪያ በስተቀር፣ ከምዕራብ አገሮች በተሸለ ሁኔታ "የሚሰጉት" ይህ ነው የሚባል የተሸለ የገንዘብም ሆነ የቴክኖሎጂ ወይንም "የቸሩታ" 'ዕርዳታ' የላቸውም:: እንዲያውም ብዙውን ጊዜ የምዕራቦቹ ተሸሎ የሚገኙበት ሁኔታ አለ:: የጦር "ዕርዳታንም" በመመልከትው፣ ሶቭየት ህብረት "ዕርዳታውን" የምትጠቀምበት አገሮችን ልክ እንደካፒታሊስት አገሮች ጥገኛና ቅኝ ተገዢ ለማድረግ እንጂ ሌላ አይደለም:: በዚህም አንፃር፣ ከዚህ በላይ እንዳመለከትነው፣ የጦር ዕርዳታዋን ባንድ በኩል፣ ባገሮችና ባካባቢዎች ላይ የወታደራዊ ተፅዕኖዋን ለማንገሥ ስትጠቀምበት፣ በሌላው በኩልደግሞ፣ አያንዳንዱን ጥይት ባይቁር በውጭ ምንዛሪ እየተቀበለች ከፍተኛ ጥቅም ታገኝበታለች:: በዚህ ከንውን ውስጥ የሚጉዳውንና የሚጠቅመውን ብሎም ተከታዩን መዘዝ ለመለየትና ለመረዳት ብዙም አስቸጋሪ አይደለም::

ከመጀመሪያው፣ ሶቭየት ህብረት የውጭ ምንዛሪ እየደለበ ቢሄድ፣ የኛው እየመነመነ ይሄዳል:: ይህም፣ ቢያንስ የሚከተሉትን ሶስት የኢኮኖሚ ሁኔታ ውጤቶችን ያስከትላል:: አንደና፣ እና ሸቀጦችን ከዓለም ገበያ ለመሸመት የሚናረን አቅም ይሟሸሻል:: ሁለተና፣ "ከድጡ ወደ ማጡ" እንዲሉ፣ የሚጉድለንንና አስፈላጊ የሆነውን የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ከሌሎች ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶችና መንግሥታት ዘንድ የውጭ ምንዛሪ ብድር እንድንጠይቅና የባሰውን ከሌላ ዕዳ ውስጥ እንድንገባ እንገደዳለን:: ይህ የመጀመሪያው ዙሪያ ጥምጥም ነው::

ይህም ሆኖ፣ የውጭ ምንዛሪን የሚያበድር ወይንም ሸቀጦችን በዱቤ የሚሸጥ ማግኘትም ቀላል አይደለም:: ምክንያቱም፣ አገሪቱ በሶቭየት ህብረትና በተቀጥላዎቿ አገሮች በተተበተበችበት ሁኔታ፣ ለማንም ዓለም አቀፋዊ የገንዘብና የንግድ ድርጅት አስተማማኝ ይዞታ የላትም:: ዛሬ አንዳንድ የምዕራብ ካፒታሊስት መንግሥታት "ዕርዳታ" ቢሰጡ፣ ነገ ከሶቭየት መንጋጋ ብትላቀቅ በሚል ምክንያት ብቻ እንጂ፣ በተስፋፊዎቹ ቅጥር መንግሥት ላይ ተማምነው አይደለም::

ይሁንና፣ ሶቭየት ህብረትና ተቀጥላዎቿ አገራችንን በቅኝ ገዥነት [illegible]

"የዓይነት ንግድ ልውጥ" የሚባለው ለምሳሌ ቡናን ለጭነት መኪና ወይንም ለሌላ ሸቀጥ በመለወጥ የሚካሄደን ንግድ ማለት ነው:: በቅድሚያ፣ በጦሩ ዕዳ በኩል ያለውን ትርጉም እንመልከተው::

የጦር ዕዳው ከዚህ በላይ እንዳልነው፣ በውጭ ምንዛሪ የሚከፈል ነው:: ታዲያ ይህንን ለመወጣት የሃገሪቱ የዓለም አቀፍ ገበያ ንግድ መጠመርና ብሎም የውጭ ምንዛሪ ይዞታችን ማደግ ነበረበት:: ይህ ቢሆን፣ ዕዳውን በተመጣጣኝ በጥር ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ለመጨረስ የሚያስችል ሁኔታ በተገኘ ነበር:: ሆኖም፣ የረጅም ጊዜ የዘረፋና የቁጥጥር ዕቅድ ያላቸው የሩስያ ተስፋፊዎችና አጋሮች እንደዚህ ዓይነቱ "የተሻለና" ከፋም ሰማም በኈራዊ ነፃነታችንን የሚያግዝ ሁኔታ እንዲኖር እንኳን አይፈልጉም:: በተያያዘ፣ ዕቅዳቸውን ከግቡ ለማድረስ እንዲችሉ በማለት፣ ለሃገራችን የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ ይሆኑ የነበሩትን ሸቀጦችን "በዓይነት ንግድ ልውውጥ" ስምምነት ስም አስቀድመው አሥረው፣ ወደነሱ አገሮች እንዲጓጓዙ አድርገዋል:: በዚህም በአንድ ወገን፣ በውጭ ምንዛሪ የሚፈጸመው የጦር ዕዳ ክፍያ ተራዝሞ እንዲቆይ የተደረገ ቢሆን፣ በሌላው ወገን ደግሞ፣ የውጭ ምንዛሪ ገቢያችን የባሰውን እየመነመነ እንዲሄድ ተደርጓል ማለት ነው:: የሩስያ ተስፋፊዎችም በዚያው መጠን ቁጥጥራቸውን የማፅናትና የማንበራፋት እምነትና ዕቅድ አላቸው ማለት ነው::

ሦስተኛ፣ የሩስያ ተስፋፊዎች አገራችንን የከተቱበት የተራዘመና መውጫ የሌለው የርስ በርስ ጦርነት በአንድ በኩል ተተኪ የጦር መሣሪያዎችን ያለማቋረጥ ከነርሱ እንድንገዛ ያስገድደናል:: ይህ በራሱ፣ ከማንወጣው ዕዳ ውስጥ በየዕለቱ በጠነጠ እየነከረንና የሃገሪቱም የጦር ጥገኝነት እየተጠናከረ እንዲሄድ ቢያደርግ፣ በሌላው በኩል ደግሞ፣ ለመሣሪያ መለዋወጫና እድገት እየተባለ የምንከፍለው ዕዳም በቀላሉ የማይገመት እንደሆነ ከፍ ብለን በሰፊው አይተናል:: እንመለስበትም:: ነገሩ በጥሩ፣ ደጋግመን እንደገለፅነው እንኳን ተከፍሎ ተቆጥሮም የማያልቅ እየሆነ፣ ሃገራችንም "በዓለም አቀፍ ዊነት" ስም በወሰዳገዶ የተያዘች አገር ሆናለች ማለት ነው::

ለ/ የኢኮኖሚው ግንኙነትና "ዕርዳታ"

የዜና ማሰራጫዎችና የመንግሥቱ ቀንደኛ ተጠሪዎች፣ የምሥራቅ አገሮች ስለሚያደርጉልን የኢኮኖሚ "ዕርዳታ" የማይለፍልፉት ነገር እንደሌለ ሁሉ ሕዝብ ያውቀዋል:: በርግጥም ደግሞ፣ "ዕርዳታ፣ ድጋፍ፣ ስጦታ፣ ብድር...ወዘተ" እያሉ ከቅጥር መንግሥታቸው ጋር ብዙ ውሎችን ፈርመዋል:: ከሚያዝያ 1969 እስከ ታህሣሥ 1972 ድረስ ብቻ እንኳን 89 የሚሆኑ የንግድ፣ የቴክኖሎጂ፣ የአየር ትራፊክና ሌሎች ሌሎች ልዩ ልዩ "የትብብር" ውሎች ተፈርመዋል:: እንዲያም ቢል፣ በየባምንቱ የሚዥርፈው የምሥራቅ ሃገሮች ሸማምነት አንድ በስምምነት ውል የሚታሰር ነገር በኩሉ ደጥር ባይደዝ እንደማይመጣ የታወቀ ነገር ነው:: የሚያስገርመው እንበልና ደግሞ፣ የሩስያ ተስፋፊዎች መንግሥትና ተቀጢሳዎቹ ሃገሮች ቅምጡን መንግሥታቸው አብዛኛውን የኢኮኖሚ ውል ያስፈረሙት፣ ስለኢኮኖሚ ምንም የማይገባቸውን የደርግ አባሎች በጥያቄ እየደለሉና በነጭ ውሸት እያታለሉ ነው:: እነርሱ ግን፣ በመሣሪያ ዕዳ ያውተበተቡትን አገር በኢኮኖሚ ቁጥጥር ሥር የሚያደርጉት በቅድሚያ አቀነባብረው በሚፈጸሙት የአጭርና የረጅም ጊዜ ፕላን እንጂ እንዲሁ በመሰ ምት እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: መመሪያ የሚያደርጉቸው የሚከተሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች ለመጥቀስ ይቻላል::

አንደኛ፣ በየትኛውም ክፍለ ኢኮኖሚ ቢሆን በተቻለ መጠን፣ አዲስ ኢንቨስትመንት የሚጠይቅ ፕሮጀክት ውስጥ ምንም አይነት ተሳትፎ አለማድረግ፣ ከተደረገም ከፍተኛ የወለጅነት ዋና በሚያጣውት ደረጃና ገዲታ በሚያስገባ ሁኔታ /የመሣሪያ ዕዳ ክፍያ../

ሁለተኛ፣ በሃገሪቱ ውስጥ የበላይነት ያለውን ዋና ዋና ቲኒቀባያሽን ካፒታል ማዳከም፣ ማጥያትና መተከት /ኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ እርሻ.../፣ ይህን ካፒታል የሚያንቀሳቅሱ ድርጅቶችንም ቢያስፈልግ ማፈራረስ፣ ወይንም ሽራባቸው ቁጥጥር ሥር ማድረግ፣ በዚህም ጠቅላላ ኢኮኖሚውን መቆጣጠር /ከሃገሪቱ የኢኮኖሚ ፕላን አንስቶ እስከ ውጭ ንግድ ድረስ/

ሦስተኛ፣ ቀደመው በተደራጁ የማምረቻ ድርጅቶች፣ በተለይም የተፈጥሮና ጥሬ ዕቃ በሚያወጡ ድርጅቶች /ከባድ ኢንዱስትሪዎች/ ላይ ማተኮር፣

አራተኛ፣ በሃገሪቱ ውስጥ ለመሪቱ የሚችሉ ጥቂት ውጤቶች ላይ የተቀመሆን፣ ሃገሪቱ የሚያስፈልጋትን በማቅረብም ብቻ ሞኖፖል መያዝ /ኤክስፖርት ሞኖፖል/ ማለትም የውጭ ንግድን በቁጥጥር ሥር ማድረግ ... ናቸው::

በዚህ ዛሬ የሩስያ ተስፋፊዎች የኢኮኖሚ ተጽዕኖዎቻቸውን ካጠነከሩ በኋላ፣ በአጠቃላይ የሃገሪቱ ኢኮኖሚ፣ በተለይ ደግሞ በቁጥጥራቸው ሥር የገቡት የማምረቻ ድርጅቶች.. የመጀመሪያ ግዴታ ሃገሪቱ ለነርሱ የገባችበትን ዕዳ እነርሱ ራሳቸው በሚወስኗቸው ሁኔታዎች መክፈል ብቻ ይሆናል:: የኢትዮጵያ የምርት ውጤቶች በዚህ ዛሬ ከእርሻ ምርት ከስንዴ አንስቶ እስከ የማዕድን ውጤት ወርቃችን ድረስ ያሉት በ"ዓይነት የንግድ ልውውጥ" ወደ በሶቭየት ሀብረትና ተቀጢሳዎቿ አገሮች ተግዘዋል:: ይጋዛሉ::

እንግዲህ በዚህ ዛሬ የሩስያ ተስፋፊዎችና ተቀጢሳዎች ከመጀመሪያው የኢትዮጵያን የማዕድንና የኢንዱስትሪ ሃብት በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ በቀላሉ የማይገመቱ እያሌ እርምጃዎችን ወስደዋል:: ለምሳሌም ያህል፣ የአደሰውን የወርቅ ማዕድን፣ የቤንዝንና የዘይት ፍለጋን፣ የመተሃራውን የስኳር ፋብሪካ፣ የድሬደዋውን የሲሚንቶ ፋብሪካና የባህርዳሩን ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ለመጥቀስ ይቻላል:: እነዚህ የኢኮኖሚ መስኮች በእነርሱ ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ከተደረገ ረዥም ያለ ጊዜ አልፏል:: በውጭ ንግድም በኩል፣ ሃገሪቱን የሸቀጣቸው ማራገፊያ በማድረግ ከፍተኛ ዘረፋ ማካሄድ ከጀመሩ ቆይተዋል:: በዚህ አንፃር፣ እንዳንዲ ዕጅ ይዘው ማስፈረም እስኪቀራቸው ድረስ አ...ያንኑ የቅጥር መንግሥታቸውን በርካታ ሃገራችንን የሚጎዱ ውሎችን እንዲያስፈርሙት በየመስኩ ያሉት ባለሙያዎች ሁሉ ያውቃሉ:: ለምሳሌም ያህል፣ ለምሥራቅ ጀርመን የተሰጠውን የአሰብ ወደብ ማስፋፋት ሥራና ለቼኮዝላቫኪያ መንግሥት የተሰጠውን 130.000.000 ብር የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ማቋቋሚያ /ከንበልቻ ደቢ አጠገብ/ ውሎች ለመጥቀስ ይቻላል:: ሌሎች ብዙዎችም አሉ:: እነዚህ ውሎች የተፈረሙት፣ በተመናቸውና በውል ግዴታቸው ምንም እንኳን እንዳንድ የናጠጡ የካፒታሊስት ሃገሮች ከሚያቀርቡት አራት አምስት ጊዜ የበለጠም ቢሆኑ ነው::

የባሰም አለ እንጂ፣

"ሸቀጥ አምጥተናል፣ አሰብ ደርሷል፣ ያስፈልጋችኋል፣ ውሰዱ" እየተባለ ያለአንዳች ቅድሚያ ውልና ግዴታ በየጊዜው የሚ...ፈውም ሸቀጥ ጥቂት አይደለም:: ባለሙያዎችና ሀሊና ያላቸው ባለሥልጣኖች "መቼ ጠየቅንና? መቼ ተስማማንና?" ብለው ለመጠየቅ መብትም የላቸውም:: የጠየቁም ቢኖሩ "ዓለም አቀፍ ዊነት ነው" እየተባሉ በቅጥሩ መንግሥት ትዕዛዝ እንዲረከቡ ተደርገዋል:: በዚህ አንፃር፣ ለምሳሌም ያህል፣ ምሥራቅ ጀርመኖች አምጥተው ያራገፏቸውን ትራክተሮች ለመጥቀስ ይቻላል:: ከዚህ በተያያዘ፣ የሚያራግፏቸን የማምረቻ መሣሪያዎችም ሆኑ አላቂ ሸቀጦች በመጀመሪያ ላይ ረከስ ብለው ከገቡ በኋላ፣ የኋላ ኋላ መዘዛቸው ብዙ እንደሆነም ከልምዱ የታወቀ ነገር ሆኗል:: አንደኛ፣ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ለብልሽት ይበቃሉ:: ሁለተኛ፣ የመለዋወጫ ዕቃቸው ዋጋ እጥፍ ድርብ ሆኖ ይገኛል:: ሦስተኛ፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ የመሣሪያዎቹም ሆነ የመለዋወጫ ዕቃዎቹ ዋጋ ህዝቡ እንደሚለው "እንደ ስፑትኒክ" ተተኩሶ ይቀርባል:: በዚህ ዛሬ ብቻ የሚፈጸመው ዘረፋና ብዝበዛ እጅግ ከፍተኛ ነው::

እንዲያም ቢል፣ የውጭ ንግዱም አጠቃላይ ሁኔታ አለ:: የዚህን መስክ ሁኔታና የፖለቲካ ትርጉም ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ አማካኝነት ልንረዳ እንችላለን:: ሠንጠረዡ የሚያሳየው በ1968/70 መካከል የተከናወነውን የንግድ ልውውጥ ቢሆንም፣ የጦር መሣሪያን አይጨምርም::

ከ1968/70 ከምሥራቅ አገሮች ጋር የተደረገው የንግድ ልውውጥ /በሚልዮን ብር

| ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡት | | | | ኢትዮጵያ የላከችው | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1969 | 1970 | 1971 | /// | 1969 | 1970 | 1971 |
| 24.471 | 36.802 | 48.486 | /// | 10.531 | 104.835 | 53.580 |

1969 ዓ.ም.ን እንደመነሻ ብንወስደው፣ ይህ ሰንጠረዥ /የጦር መሣሪያን ሳይጨምር/ በሶቭየት ሀብረትና ተቀጢሳዎቿ አገሮች ወደ ሃገራችን የሚያራግፉት ሸቀጥ ከ1969 ዓ.ም. እስከ 1970 በ50 ከመቶ፣ እስከ 71 ዓ.ም. ደግሞ በ98.1 ከመቶ እንደጨመረ ያመለክተናል:: በአንፃሩ ደግሞ እኛ የላክነው ከ69 ወደ 70ዓ.ም. በ89.4 እጅ፣ ወደ 71 ደግሞ፣ በ411.3 እጅ ተመንድጓል:: በጥሩ እንግዲህ፣ አንደኛ፣ የውጭ ንግዳችን በጥቂት ጊዜ ውስጥ ከበሶቭየት

በቀድሞው መንግሥትና በሶቭየት ህብረት መካከል በ"ዕርዳታ" ስም የተደረገውን የ
170— ሚሊዮን ብር ብድር ይመለከታል:: ታሪኩንም ለመጀመር 20 ዓመታት ወደ
ኋላ መመለስ ያስፈልጋል::

እንደሚታወቀው፣ በሃምሌ ወር 1951 ዓ.ም.፣ ሃይለሥላሴ በሶቭየት
ህብረትን ለመጎብኘት ሄደው ነበር:: በዚያ በተደረገው ስምምነት መሰረትም፣ ሶ
ቭየት ህብረት ለኢትዮጵያ የ250— ሚሊዮን ብር ብድር ልትሰጥ ቃል ተገባለች::
ብድሩ፣ ለአንድ ዓመት ከከፍያ ነፃ ሆኖና በ2.5 ከመቶ ወለድ በ12 ዓመት ው
ስጥ ተመልሶ እንዲከፈል በተደረገ ስምምነት መሰረት የተሰጠ ነበር:: ይሁን እ
ንጂ፣ የ12 ዓመቱ የውል ዘመን ቢያልቅ /ማለትም እስከ 1963 ድረስ/ የሃይ
ለሥላሴ መንግሥት ከብድሩ ውስጥ የተጠቀመው 25 በመቶ /56—ሚሊዮን ብር/ የ
ሚሆነውን ብቻ ነበር:: ከዚህም ውስጥ፣ 26 ሚሊዮኑ የአሰብን የቤንዚን ማጣሪ
ያ ለማቋቋም ቢውል፣ 30— ሚሊዮኑ የሚሆነውደግሞ "ኢትዮ—ሶቭየት የንግድ ኩባ
ንያ" የተሰኘውን የሶቭየት ህብረት የውጭ ንግድ ማስፋፊያ ድርጅት ለማቋቋሚያ
ውሎ ነበር::

የውሉ 12 ዓመት እንዳለቀ፣ የሃይለ ስላሴ መንግሥት ቀሪውን ብድ
ር በመጠየቅ ሁለተኛ ስምምነት ይፈራረማል:: የሁለተኛው ስምምነት የውል ግዴታ
ዎችም ልክ እንደመጀመሪያው ውል /በ2.5 ከመቶ ወለድ በ12 ዓመት እንዲከፈል/
ነበሩ:: ይሁን እንጂ፣ ከ1963 — 1968 ዓ.ም. ድረስ፣ ከ1951ዱ ጠቅላ
ላ ብድር ውስጥ የተሰለፈው ገንዘብ ከ30 በመቶ /75— ሚሊዮን/ ባይበልጥ ይ
ቀራል:: 375 ሚሊዮን የሚሆነው በሶቭየት ህብረት ዕጅ ውስጥ ያለ ነበር ማለ
ት ነው:: በመሆኑም፣ ቀሪውን ብድር ለመጠየቅ በሃምሌ 1968 አንድ የደርግ
ቡድን ወደ ሞስኮ ይሄዳል:: ሆኖም፣ ከዚህ በላይ እንዳመለከተነው፣ ሶቭየት ሀ
ብረት በዚያን ወቅት የኢትዮጵያን አብዮት ከሚወጉ ሃይሎች ጋር ከመልከስከሷም
በላይ፣ ገና በመሣሪያ ዕዳ ኢትዮጵያን ስላላወተበተበች ቀሪ የተባለውን ብድር
ለመስጠት ፈቃደኛ ባትሆን ቀረች:: ቡድኑም በደ እጁን ተመለሰ:: ሶቭየት ሀ
ብረት፣ ገና ከ20 ዓመታት በፊት ለሃይለሥላሴ የገባቸውን ውል "አሟልታ" ለመ
ፈጸም ፈቃደኛ የሆነቸው፣ ይልቁኑ ደርግን እጇ ውስጥ ማስገቢቷን ካረጋገጠች በ
ኋላ ሆኖና፣ ከዚህ በላይ ያወሳነውን የ170— ሚሊዮን ብር ቀሪ ብድር ለመልቀ
ቅ ወሰነች:: ስንት መዓት መገባ የወረደለት "ዝነኛው" የሚያዝያ 1971 ዓ.ም.
ውልም ተፈረመ::

ነገር ገን ሶቭየት ህብረት ለ"ሶሽያሊስቷ" ኢትዮጵያና ለ"ኮሚኒስት"
መሪዎቿ /ምን አለፋን ለቀድሞ መንግሥቷ/ የሰጠችው "ሶሽያሊስታዊ ዕርዳታ"፣
ከ20 ዓመታት በፊት ለአፄ ኢትዮጵያ ከሰጠችው "ዕርዳታ" ትሪሪ ቢሆን፣ ከ
ቶም በምንም የሚለይ አልነበረም:: ምክንያቱም፣ የሚያዝያ 1971 ውል ሃይለሥ
ላሴ ከ20 ዓመት በፊት ከተዋዋሉት ስምምነት በምንም ባይለይ፣ ያው ለአንድ ዓ
መት ከከፍያ ነፃ ሆኖ፣ በ2.5 ከመቶ ወለድ በ12 ዓመት ውስጥ ተከፍሎ እንዲ
ጠናቀቅ የሚያስገድድ ውል ነበር:: እንዳውም ጉዳት አለው እንጂ:: ምክንያቱም፣
በገንዘብ አቅምነቱ ሲተረጎም፣ ለአፄ ሃይለሥላሴ ተሰጥቷቸው የነበረው በልጦ አ
ለው:: የዚያን ጊዜውና የዛሬው ገንዘብ በፍጹም ሆነ በተመጣጣኝ የመግዛ አቅ
ማቸው ትይዩ አይደሉም:: የዛሬው ገንዘብ የመግዛ አቅም ዝቅተኛ ነው:: በ12
ዓመት ውስጥ ከነወለዱ ሲከፈል ደግሞ፣ ወደ ሶቭየት ህብረት ካዝና የሚፈሰው ገ
ንዘብ የትርፍ ትርፍ ይሆናል::

በጥሬ እንገዳሀ፣ ሶቭየት ህብረትና ተቀጢሳዎቿ አገሮች፣ በ"ሶሽያ
ሊስታዊ" የኢኮኖሚ ግንኙነትና "ዕርዳታ" ስም ከዛሬው የቀድሞ መንግሥታቸው ጋ
ር የሚጠቀሉት፣ አገራችንን በበለጠ በነርሱ ተፅዕኖና ቁጥጥር ሥር ለማዋል እን
ጂ፣ በውነትስ ህዝባችን ከድህነቱና ከችጋሩ ተላቅቆ በልጽገና እንዲኖር ተመኝተ
ውለት አይደለም:: በጥር በጥሬ ከፍ ብለን ያየናቸው ጉዳዮች ይህን በሚገባ የ
ሚያረጋግጡ ናቸው::

በገሃዱ እንደሚታወቀው፣ ሃገራችን ዛሬ ከ5 ሚሊዮን በላይ ረሃብተ
ኞችን ይዛ በመማቀቅ ላይ ትገኛለች:: በዚህ ወቅት እንኳን፣ የነርሱ "ዕርዳታ"ያው
በዘመዘ ነው፣ በበዓዊ እርዳታቸው ከቁጥር የሚሰፍር ሆኖ አልተገኘም:: በ
ተቃራኒ፣ የሃገሯት የርሻ ምርቶች ወደነርሱ ይፈሰሉ:: ስንዴያችን....ከዱንች
እስከም ከቸርቻር ገበያ እየተለቀሙ ይጋዛል:: ጤፋችንም ባይቀር "ለፈረንጅ ይ
ሆን እንደሁ፣ ሸረ ይሺ ነገር ይጠና" ተብሉ እየተመኙት ነው:: ይልቁንስ፣ የነ
ርሱ 'ሰብዓዊ' ዕርዳታ ቀርቶብን ፣ ለነርሱ 'ኢክስፖርተሮችና አማካሪዎች' ለአንበሳና



ና ከተቀጢሳዎቿ አገሮች ገበያ ጋር በከፍተኛ ደረጃ ተሣሥሯል:: ሁለተኛ፣ ይህ
በራሱ ለኢኮኖሚ ቁጥጥርና ለፖለቲካ ተፅዕኖ የሚያመቻቸውን የበላይነት ሁኔታ
ፈጥሮላቸዋል:: ሦስተኛ፣ ከዚሁ በተያያዘ፣ የሃገሪቱ ዓለም አቀፋዊ የንግድ ግን
ኙነት እየጠበበና አገሪቱ ወደ ኢኮኖሚ ብቸኝነት እያመራች በመሄድ ላይ እንደም
ትገኝም እንረዳለን:: በቀለሉ ለማየት እንደሚቻለው የሃገራችን የውጭ ንግድ ወ
ደ ምሥራቅ አገሮች የዞረው፣ ከሌሎች /በተለይም ከምሥራቁ ዓለምና ከገለልተኛ
አገሮች/ ጋር ይከናወኑ የነበረትን የንግድ ልውውጦች በማቀዛቀዝ ወይንም ጠርበ
በማዓፈን ነው:: ብሎም፣ በዚህም ደረጃ ጭምር፣ የሃገሪቱ ገለልተኝነት ሽታው
እንቧን እየጠፋ እንደሄደ እንገነዘባለን::

በዚሁ የንግድ ልውውጥ ሥር፣ ቀደም ሰንል ያነሳነው "የዓይነት ነገ
ድ ልውውጥ" ጉዳይ ደግሞ፣ ራሱን የቻለ ስፍራ ይዞ ይመጣል:: ይህንው የንግድ
ልውውጥ ዘይቤ፣ የሃገሪቱን ዓለም አቀፋዊ የንግድ ግንኙነት ከመሰበሩና የሃገሪ
ቱን የውጭ ምንዛሪ ገቢ ከመቀነሱም በላይ፣ ባንድ በኩል በልዋጭ ስም በሚመጡት
ሸቀጦች ምክንያት የሚደርስብንን መጉዳትና፣ በሌላው በኩል ደግሞ፣ እነርሱ ከእ
ና በዓይነት ለውጥ ስም የሚወስዱትን ሸቀጥ አዞረው በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ
በመሸጥ የሚያገኙትን ጥቅም ስናስተያየው፣ ራሱን አስይዞ የሚያስጨንቅ ጉዳይ ሆኖ
እናገኘዋለን:: እንደዚህ ዓይነቱ ነገር፣ በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ "የቦስት
ማዕዘን ንግድ" ተብሎ ይታወቃል:: ኢትዮጵያን በመመለከተው፣ ከምሥራቅ ጀርመን
ጋር የተደረገውን አንድ "የዓይነት ንግድ ልውውጥና"ውጤቱን ብቻ አብይተን እን
ለፍ::—

በ1970 መጀመሪያ ገደማ ላይ ነው:: በቀድሞው የኢትዮጵያ መንግሥ
ትና በምሥራቅ ጀርመን መካከል፣ ኢትዮጵያ ወደ ምሥራቅ ጀርመን በየዓመቱ 10.000
ቶን ቡና ልትልክ፣ ምሥራቅ ጀርመን ደግሞ በምትኩ ልዩ ልዩ የኢንዱስትሪ ምርቶ
ችን እንድትልክ አንዳች ዓይነት ስምምነት ይደረጋል:: ነገር ግን ፕሮቶኮሉ ከ
መፈረሙ በፊት፣ ኢትዮጵያ 5.182 ቶን ወደ ምሥራቅ ጀርመን ልካ ነበር:: ፕ
ሮቶኮሉ በተፈረመበት ጊዜም፣ ወደ ምሥራቅ ጀርመን የተላከው ቡና 14.766 ቶ
ን ደርሶ ይገኛል:: ለዚያውም፣ በፖለቲካ ምክንያቶች የተነሳ፣ ዋጋው በዓለም
አቀፍ ገበያ ተመን ባይሆን፣ "የርዳታ ዋጋ" በሚል በዝቅተኛ ተተምኖ እንዲላወ
ጥ ነበር ስምምነቱ የተደረገው::በምትኩም፣ "በየፈፋው ተደፋ" ተብሉ የተሰ
የመው ሃይፋ /ሕይ ኪፋ ኢ ደብለው ሲስ እ/ የተሰኘው ካሚዮንና ዚቲ የሚባለው
ትራክተር ይገባሉ:: ውጤቱ ምንድን ሆነ??

ምሥራቅ ጀርመን ከኢትዮጵያ "በወዳጅ ዋጋ" ያስጫነችውን ቡና በጥ
ቂት ጊዜ ውስጥ አባልዋ ለምዕራብ ጀርመን በዓለም ገበያ ዋጋ ተመን ሸጠች::
በዚህም፣ በንዱ ወገን በዋጋው ልዩነት እንኳን ብቻ ከፍተኛ ጥቅም ስታገኝ፣ በ
ሌላው ወገን፣ በውጭ ምንዛሪዎ ገቢዋ ከበረች:: ኢትዮጵያ ግን፣ በውነትም በየ
ፈፋው እየተደፋ ባለቀት ተሽከርካሪዎች ከኪሳራ ውስጥ ገባች:: የውጭ ምንዛሪ
ገቢዋን አጣች:: አልፎም፣ ከጥንት ጀምሮ የቡና ደንበኛ በመሆን ሲያገለግላት
የነበረውን የምዕራብ ጀርመን ገበያ፣ አባልፋ ለምሥራቅ ጀርመን አቀበዮች አስረ
ከበች:: ... መቼ በዚህ አለቀ?..

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቀድሞ መንግሥት፣ "በትርፍ የለኮነውን ቡና እ
ንተባበበ፣ ቢሆን ችግርም አለብንና ለቤንዚን መግዣ እንዲሆነን በውጭ ምንዛሪ
ስጡን ፣ ያለዚያም ለሶቭየት ዕዳችን ማቻቻያ እንዲሆን ወደዚያው ይከፈልልን"
በማለት የልመና ጥያቄ ለምሥራቅ ጀርመን አስገብቶ ነበር:: እነርሱ ግን ምን
ገዷቸው ፡ "ቢገኛችሁ ሌላ ሸቀጥ በምትኩ ውሰዱ" ብለው መለሱ:: የተላከው ቡዱ
ን በምትኩ ሊወስዱ የሚችለውን ሸቀጥ አፈላልገ ተባለ:: ምንም የሚያረካውን ሸ
ቀጥ ባያገኝ ይቀራል:: በመጨረሻያም፣ በበሰበሰ የጋስታ ኪምር ተሰማምቶ የምሥ
ራቅ ጀርመን ማኩርኒ ቢራገፍብን ከረመ....::

እንደዚህ ዓይነቱ ያልተመጣጠነና ሃገራችንን የባዕድ አገሮች ጥቅም
ተንከባካቢ አድርጎ የሚያስቀር የኢኮኖሚ ግንኙነት፣ በዕኩልነት፣ በጋራ ጥቅምና
በመረዳዳት ላይ ከሚመሠረተው በሶሽያሊስታዊ የኢኮኖሚ ግንኙነት ጋር እንዳችም መ
ቀራረብ የለውም:: በተቃራኒ፣ በዘረፋና በተዘረፊ፣ በገዢና በተገዢ፣ አያን:
ሃገራችንን ወደ ቅኝ ገዛትነት የሚያዘቅጥ የኢኮኖሚ ግንኙነት ነው፣ከዚህ በገ
ሃዱ ከሚታየውአልፈን፣ "ብድር፣ዕርዳታ፣ ስጦታ" ወደሚባሉት የተሸጋገርን እንደሆ
ን ደግሞ፣ ነገ ጠበ በቀድሞ መንግሥትና በአገሮቹ መንግሥታት የሚለረፈው ሁሉ

ተነበሬተተ ቢሮክራሲው ጉያ ውስጥ ለመከተት እየተሽመደመደ ነበር:: በህዝቡ ሰይ ከመተማመን ይልቅ በቢሮክራሲውና በውጭ ሃይሎች ላይ እምነቱን እየጣለ ነበር:: በዚህ ሂደት ውስጥ፣ የአብዮቱ ወገኖች ደግሞ በራሱ በ"አብዮቱ"ና በ"ሶሽያሊዝም" ስም እየተመቱና እየተጠረጠሩ ነበር:: የኢትዮጵያ ፀረ ህዝቦች፣ ከተስፋፊዎች አቀጣጠም ሆነ ከቀኝ ሃይሎች፣ከዚህ የበለጠ የሚፈልጉት ነገር አልነበረም:: ተባከተሰችዋል::

ቀደምውንስ ቢሆን፣ አገርና ወገን አፍቃሪ የሆኑትን ሃቀኛ ተራማጆች፣ ዲሞክራቶችና ብሄርተኛ ሃይሎችን ባይጠፈጥፍ፣ ባያኮምና ባይበትን በኢትዮጵያ ላይ የበላይነትን ሊያነግሥ የሚችለው የውጭ መንግሥት የትኛው ነው?? ፀረ አብዮትንስ ለበሬ የሚችለው ፀረ አብዮት የትኛው ነው??........የራስያ ተስፋፊና ጣልቃ ገብ መንግሥትም በዚህ ልዩ አልሆነም:: ውጤቱ ተናገሯል::

"ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሬፐብሊክ ለማቋቋም" የሚታገለው የኢትዮጵያ ህዝብ በወታደራዊ አምባገነን አገዛዝ ሥር ወደቀ:: "ነፃና ጠንካራ የሆነ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት" የሚታገለው የኢትዮጵያ ህዝብ በራስያ ተስፋፊ መንግሥትና በተቀጥላዎቹ አገሮች የሚበዘበዝና የሚመዘበር ሆነ:: "የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች አንድነት በእኩልነት፣ እርስ በርስ በመረዳዳት፣ በወንድማማችነትና በመፈቃቀዱ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን" የሚታገለው ህዝብ ትምክህተኞች ናጥጠውበት ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ማለቂያ ከሌለው የርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ተከተተ:: "የኢትዮጵያ ሠራዊት የሃገሪቱን ነፃነት፣ አንድነትና በሰላም ለመጠበቅ በሚያስችለው ሁኔታ ለማደራጀት" የሚታገለው ህዝብ፣ ሠራዊቱ በራስያ ተስፋፊ መንግሥት ተፅዕኖና ቁጥጥር ሥር መውደቁን ማየት በቃ:: "የሃገሪቱ የውጭ ፖሊሲ በታወቁት የገለልተኛ አገሮች መርሆች ላይ ተመሥርቶ እንዲመራና ሃገሪ ዕውነተኛ ገለልተኛ አገር እንድትሆን" የሚታገለው ህዝብ፣ ገዢዎቹ በውስጥ ቅጥር መንግሥት የሆኑትን ያህል፣ በውጭ ደግሞ በየደረሱበት የራስያ ተስፋፊ መንግሥት አፈ ቀላጤና ገንቦ ቀዳሚ አጠብጣቢዎች መሆናቸውን ለመስማትና ለማየት በቃ:: በመጨረሻም፣ "ኢሠፓአኮ" የተሰኘው የአድርባዮች፣የትምክህተኞችና የቢሮክራቶች ድርጅት ብቅ ነበተ::

ነገሩ ግልፅ ነው:: ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ፣ የራስያ ተስፋፊዎች በንዱ በኩል፣ የኢትዮጵያ አድርባዮችና ፀረ አብዮተኞች በሌላው በኩል እየተሳሰሩ የየልባቸውን አድርሰዋል:: የትግል ፍልሚያውም፣ በዛሬው አገዛዝና በራስያ ተስፋፊ መንግሥት በንዱ ወገንና በሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ በሌላው ወገን እንደሆነ የዚያኑ ያህል ግልፅ ሆኗል:: ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ ለዲሞክራሲና ለብሄራዊ ነፃነት የሚያደርገውን ትግል የሚቀጥለው በዚሁ አቅጣጫ ነው::

ለ/ የተሟላ የፖለቲካ ቁጥጥር

የራስያ ተስፋፊዎች የደርግን መሪዎች ከኪሳቸው ለመከተት ሲገበገቡ /ከሻ አለቃ ለገሰ ጀምረው በሻለቃ መንግሥት እስከጨረሱ ድረስ/፣ ዋና አቅዳቸው የነበሩ ቅምጥና ተገዢ የሆነ መንግሥትና የፖለቲካ ድርጅት ለመፍጠር ነበር:: በሚያዝያ ወር 1969 ዓ.ም. በሻለቃ መንግሥቱ ሃ/ማርያም የሚመራው ቡድን ሞስኮን ሲጎበኝ በ[illegible]የተሰጠው ምክርና ትእዛዝ "በተቻለ መጠን አንድ ወጥ የሆነ ፓርቲ አቋቁሙ፣ በዚህ ፓርቲ አመራር ሥር ለምታደርጉት ሠራዊት ማንኛውም መሣሪያ እንሰጣችኋለን " የሚል ትዕዛዝ ነበር::

ከዚህ ጊዜ በኋላ የበደሉ ኩሊክ [illegible]ራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምን ተቃውሞ መጀመሪያ ኢማሌዲህን እንዴት እንዳኮላሸውና እንደበተነው፣ ከዚያም በኋላ እንዴት ወደ "ኢሠፓአኮ" እንዳመራ አገር ምድር ያውቀዋል:: እንደተጠበቀው "ኢሠፓአኮ" የተሰኘውን ጉድ ደግሞ፣ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻው በበላይነት በመቆጣጠር ያደራጁት የራስያ ተስፋፊዎችና ተቀጣዮች ነበሩ:: የመቀፈን ቅርፅ የሰጡት፣ "የታወቀው" ራስያዊው ሽሬዋ /በነገራችን ላይ ኢህአፓም በመሠረት ያገዝ የነበረ የኬጂቢ በላይ/ እና እንደ ኩባያዊ ራኦል ቫልዲብ ቢ የመሳሰሉት ሰዎች ናቸው:: ኢትዮጵያዊያንን በሚመለከተው፣ ሞስኮና ሌሎች ምሥራቅ አገሮች ውስጥ "አየነቀ" መጡ የተባሉት "ኃደች" በተሰላኪነትና ቢበዛ በአማርኛ ሥነፀሁፍ አገልግለው እንደሁ እንጂ፣ እንዳቸውም ሰፍራ አልነበራቸውም:: "ኢሠፓአኮ" ከተመሰረተም በኋላ ፣ የተስፋፊዎች ቤተበብ ውስጥ፣ "የትልቁ" ሰው— የአባወራው የብረዥነቭ ፊት በተደጋመ ቁጥር፣ የሻለቃ መንግሥቱን ፎቶ ከማየት በስተቀር ሌላ የሚሠራት ነገር የሳ[illegible] አይችሉም:: በጥራ፣ የ



ለ ነበር:: ደግመስ፣ ሰንት መዓት [illegible] ድርጅቶች ..[illegible] ነበ ን ቴክኒክና 'ኢክስፐርትነት' በየትናቸው ላይ ነፍስ ቢዘራ ታየ?? በተቃራኒው፣ ሥራ አጡ እንደ አሸን እየፈላ፣ ረሃብተኛውና ለማኙ እየጨመረ፣ ስደተኛው እየበረከተ፣ መጪው ጊዜ እየጨለመና ውል እየጠፋበት ሄዷል:: የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ለህዝቡ ጥቅም ከመዋል ይልቅ፣ ከዕለት ዕለት በበለጠ የራስያ ተስፋፊዎችና የተቀጥላ አገሮችን ኢኮኖሚ ለማዳበርና እነርሱ በሃገራችን ላይ ያላቸውን ቁጥጥር ለማጠናከር የሚያገዝ ብቻ ሆኗል::"ዕርዳታው" በድሬ ..ወዘተ. ዓይነ ያወጣ የዘረፋ መሣሪያ፣ "የንግድ ልውውጡ"፣ የንግድ ግንኙነት ሃገራችንን በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዳ፣ ጥገኝነትን የሚያጠናክርና በሎም ነፃ ህልውናችንን የሚገስ መሆኑ ታይቷል::

የራስያ ተስፋፊ መንግሥት በኢኮኖሚ ቁጥጥር ሥር ያዋለውን ሃገር በፖለቲካም ካልተቆጣጠረው ገና፣ የተሟላ እንዳልሆነ ያውቀዋል :: ጣልቃ ገብነቱና ዘረፋው በሙሉ በፖለቲ[illegible] መረጋገጥ ይኖርበታል::

5. በሃገሪቱ የውስጥና የውጭ ፖለቲካ ላይ የሶቭየት ሀብረት ቁጥጥር

የራስያ ተስፋፊ መንግሥት የረጅም ጊዜ አቅዱና ፍላጎት አንዱን ሃገር ለሱ ታማኝ በሆነ ድርጅት ቁጥጥር ሥር አስገብቶ፣ ለረጅም ጊዜ የእጅ አዙር ቅኝ ግዛቱ አድርጎ ማቆየት ነው:: ኢትዮጵያንም በሚመለከት፣ ይህ ዓላማው ግቡን እንዲመታ፣ መጀመሪያ የኢትዮጵያን አብዮት በማወጉ ድርጅቶችና ሃይሎች አካባቢ ተልከስክሶ ከዚያም ፈረስ በመለወጥ ከደርግ ጋር ሲረግጥ ቆይቶ፣ በመጨረሻ ደርግን ጫማው ሥር ጥሎ አሻንጉሊቱ ሊያደርገው በቅቷል:: በኋላም ወደ"ኢሠፓአኮ" ገሥግሷል::

ሀ/ የራስያ ተስፋፊዎች መግባትና የአብዮታችን መቀልበስ

ሃገርና ወገን አፍቃሪ የሆኑት ሃቀኛ ተራማጆች፣ ዲሞክራቶችና አርበኞች ምን ጊዜም ቢሆን የማንም የውጭ መንግሥት የበላይነት አይቀበሉም:: የማንም ሃያል መንግሥት ቡችላና ቅጥር ሆነው ለማደር አይፈቅዱም:: ይልቁኑ፣ ማንኛውንም መስዋዕትነት ተቀብለው ለብሄራዊ ነፃነታቸውና ክብራቸው ይዋደቃሉ:: እነሱ፣ ለሥልጣን ለከንቱ ክብርና ሙገሳ የሃገራቸውን ነፃነትና ክብር አሳልፈው አይሰጡም:: በተቃራኒው፣ በእርምጃቸው ፀንተውና በህዝቡ ላይ ብቻ ተማምነው እስከመጨረሻው ድረስ ለመሟሟት የተዘጋጁ ናቸው:: በመሆኑም፣ ከመጋቢት 1969 አንስቶ እስከአሁንም ድረስ ታይቶ የማይታወቅ ጭፍጨፋና ገፍ ወርዶባቸዋል::

በዚህ ጭፍጨፋና ገፍ፣ የራስያ ተስፋፊና ጣልቃ ገብ መንግሥት ጉዳይ አስፈፃሚ በመሆን ያገለገለው የሻ አለቃ ለገሰ አስፋው ከሃዲ ቡድን እንደነበር ዛሬ ለማንም የተሰወረ አይደለም:: ይህ ቡድን በአንዱ ወገን፣ ለሶቭየት ተስፋፊ መንግሥት እየሟገተ፣ በሌላው ወገን የአብዮቱን ሃቀኛ ሃይሎችና ወዳጆች እያጠፋና እየበታተነ፣ በአንዱ ወገን ብሄራዊ ነፃነታችንን እያስገበረ፣ በሌላው ወገን አብዮታችንን ኮላሽቶ እስከመቀልበስ አድርሶታል::

ከሱማሊ ወረራና ከራስያ ተስፋፊ መንግሥት መግባት አንስቶ እስከ ቀኖች ሀብረትና እስከ "ኢሠፓአኮ" ድረስ የነበረው ሁኔታ፣ የተነሱት የአብዮታችንና የነፃነታችን ጥያቄዎች የታወቁ ናቸው:: እርምጃችንንም በየጊዜው ስሰባወቅን እዚህ ላይ አንመለስበትም:: የአብዮታችን መቀልበስና የተስፋፊዎች መግባት ግንኙነትን ለመረዳት ግን አጠንክሮማስታወስ የሚያስፈልግ ቁም ነገር አለ:: ይህም፣ የራስያ መንግሥት ተፅዕኖ መጠናከርና የፀረ አብዮት መግነን ተደጋግፈው ያደጉ ክስተቶች መሆናቸው ነው:: ምክንያቶቻቸው የተለያዩ ቢሆኑም፣ የራስያ ተስፋፊ መንግሥትና የኢትዮጵያ ፀረ— አብዮት ሃይሎች በአከከልኝ ልከከልህ ፖለቲካ በኢትዮጵያ ምድር ላይ በአንድነት ለመገናኘት በቅተዋል::

በመሆኑም፣ የራስያ ተስፋፊና ጣልቃ ገብ መንግሥት በአፍሪቃ ቀንድ ተፅዕኖውን አጠንክሮ ለማሳረፍ አመቺ ሁኔታ አጋጥሞት ነበር:: ከዚህ ግቡ ለመድረስ ግን፣ እንደዚያ ራሱን በራስ ለመቻል፣ ለብሄራዊ ነፃነትና ለገለልተኝነት የሚሟገተውን የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮት መጋፈጥ ነበረበት:: ተጋፍጧል:: ለነዚህ የተቀደሱ ዓላማዎች ፀንተው የሚታገሉት ሃቀኛ ተራማጆች፣ ሃገር ወዳጆችና ብሄርተኛ ሃይሎችም ተናንቀውታል:: በሌላ በኩል ግን ለኢትዮጵያ ፀረ አብዮት ሃይሎች [illegible]

"ኢሠፓአኮ" አመሠራረትም ሆነ አሠራር የማንኛውንም አሻንጉሊት ለመሆን የታጠ ድርጅት አመሠራረትና የአሠራር ሀገን የተከተለ ነው:: የሩስያ ተስፋፊዎች የተሟላ የፖለቲካ ቁጥጥር የሚያደርጉበትን የሃገር ደላሎች የተሰበሰቡበትን የድርጅት መሣሪያ አግኝተዋል::

ሆኖም፣ የውስጡን የፖለቲካ ሁኔታ ለመቆጣጠር የሚያደርጉት ጥረት፣ የተሟላ ፍሬውን ሊሰጣቸው አልቻለም:: በጠቅላላ የፖለቲካ ተቃውሞ ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ፣ ፓርቲያቸውን ለማደራጀት መንፈራፈር ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ መሣቂያና መሣለቂያ በማድረግ እንትፍ ብሎ ተፍቷቸዋል:: ኢሠፓአኮቸውም፣ በውነትም በሰፊው ህዝብ በጠመለት — "የኢትዮጵያ ሠላጣና ፓፓዬ አምራቾች ኮርፖሬሽን /ኢሠ.ፓ.አ.ኮ/ ስም ሊጠራ ይችላል:: መሰብሰብ የቻሉት፣ በትከል 'ሠላጣና ፓፓዬ' የሚገበስሱ የሚሊተሪ— የቢሮክራሲ ቢሮክራቶችን ወይንም አይን ያወጡ አድርባዮችን፣ ያለዚያም በትዕዛዝ የሚያስገድዱትንና የሚጠሙትን ብቻ እንደሆነ "ታሪካዊው" የመጀመሪያ ጉባኤያቸው መሰከረ::

የሃገሪቱን የውጭ ፖለቲካ በመመልከት ግን የሩስያ ተስፋፊዎች የሚመኙትን አገኝተዋል:: ኢትዮጵያም "ስንተኛዋ የሶቪየት ሀብረት ጠቅላይ ግዛት ትሆን??" ተብሎ የሚጠየቅበት የሃፍረት ደረጃ ላይ ደርሳለች :: በተለይ፣ ልክ እንደጠጪላው ውሻ ተስፋፊዎችን በናገበር በዓለም አቀፍ መንጉዎች ላይ አቋም ሳንወስድ ከተፈረመበት "የሰላምና የወዳጅነት ስምምነት" ጊዜ አንስቶ፣ ኢትዮጵያ በዓለም ህዝቦች ሸንጎ ላይ ከጥር መገርቷ ቀርቷል ሊባል ይቻላል:: "ኢትዮጵያዊ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ምን አስፈለገ?" መባሉም ትክክል ነው:: የኢትዮጵያ 'ተወካዮች" ውንጥ ውንጥ የሚሉት ከሞስኮ በሚሰጣቸው የውጭ ፖሊሲ መዘዝ እንጂ፣ ኢትዮጵያን ክብርና ጥቅም ለማስከበር እንዳልሆነ አለም አውቆታል:: ከሁሉ አሳፋሪም ነገር ለለ እንጂ::

ዛሬ ሃገሪቱ ላይ የሚፈነጩት በስልጣኖቹ አገራችንን ለፍርፋሪና ለከንቱ ሙገሳ መሸጣቸው አንሶ ፣ አፍሪካንም ለማስማማት ሸር ጉዱ ይላሉ:: "ምኝ ያገኘው ፈሊጥ" እንዲሉ፣ የቻይናን መንግሥት እንዴት ሲያወግዙ እንደነበር እናውቃለን:: በሄዱበት አገሮች ሁሉ በዚህ ጥያቄ ላይ "አቋም ለማስወሰድ" በጥራዝ ነጠቅ አነጋገራቸው ሲያጉረፈ ያተረፉት ነገር ቢኖር፣ ራሳቸው መሳለቂያና መሳቂያ ሁነው፣ ሃገሪቱንም ከውርደት ላይ መጣል ነበር:: አንዴ፣ ሸለቃ መንግሥቱ ሃይለ ማርያም ለጉብኝት ታንዛኒያ በሄደበት ወቅት፣ ኒሬሬን በዚህ ጉዳይ ላይ አቋም እንዲወስዱ ጠይቋቸው ነበር:: ነገሩ አልገባ ያላቸው የተማረት ኒሬሬ ለመልሱ ግን ፣ "የሰው ዝንዝ፣ በይሆን ሁላችንም ነገር ማድረጉ ይቀርብን" ብለው በራት ግብዣና በትዝብት ግብዣ እንደሸኙት ይነገራል:: ሃቫና ተደርጎ በነበረው የገለልተኛ ሃገሮች ጉባኤም ላይ፣ ሌላው ቀርቶ ፊደል ካስትሮ ራሱ እስኪታዘባቸው ድረስ፣ "ገለልተኛ አገሮች የሶቪየት ሊስት አገሮችን ወገን መምረጥ አለባቸው" እያሉ ሲያጉረፈ ሃገሪቱን የተለመደው ትዝብት ላይ ጥለዋታል::

የአፍጋኒስታን ሁኔታም፣ ከሌሎቹ ሁሉ ይበልጥ ማፈር ከተቻለ፣ ይበልጥ የሚታፈርበት ነው:: ከዓለም አገሮች ሁሉ፣ በሶቪየት በአፍጋኒስታን የፈጸመችውን ወረራ የደገፉት 18 የሶቪየት ተቀጢላ አገሮች ብቻ ነበሩ:: ከነዚህ ውስጥ እንደቆጠረን ዓይነቶቹ በሃገርነት ስም የተመዘገቡ የሶቪየት ሀብረት ክፍለ ሃገራትና እንደ ኢትዮጵያ [illegible] ናቸው:: መጨ ነገሩ የሚያስገርምና እንዳው ቢሮ "አፈበጫ የእናትን ገበናር ይበዛል" የሚባለውን ያበቶች ተረት የሚያስታውስ ነው:: የሩስያ ተስፋፊዎች አፍጋኒስታንን ሲወሩ የተመረኮዙበት ሰበብ፣ ከወረራው ጥቂት ወራት ቀደም ብለው ከዚያች አገር መሪዎች ጋር የተፈራረሙትን የ20 ዓመት "የሰላምና የወዳጅነት ስምምነት" የተባለውን ሰነድ ነው:: እንደዚህ ዓይነቱን "ስምምነት" ደግሞ፣ የዘመኑቹን ባንዳዎች ከአፍጋኒስታን ወራሪ ከሶቪየት ሀብረት ጋር ተፈራርመውታል::

ደግሞ የዘመበበዩን ጉዳይ እንመልከት:—

የአርበኖቹ መሪዎች በለንደን አድርገውት የነበረውን ስምምነት ሶቪየት ሀብረት "ጦርነት ሊያመጣኝ ነው፣ምርጫ ከተበለ ደግሞ እኔን የማይደግፍ የመጋቢ ወገን ሊመረጥ ይችላል" በሚል ርካስ አስተባበብ ተቃውማ ነበር:: ይህን ሲሰሙ፣ የናዎቹ ቅምጦች በሱ፡ ቀበሌ "ህዝባዊ" ድርጅቶችን እየሰበሰቡ ውይይትንም፣ ስምምነትንም፣ የምርጫውንም ውጤት አንቀበልም" የሚሉ ወብኒዎችን ያጋጉዱ ጀመር::"የሬፈረት ይደርሰል" ነውና ምርጫው ተካሂዶ የመጋቢ ወገን አሸናፊውን ብሎ ብቻውን ሥልጣን ከመያዝ ይልቅ፣ እጅግ አስተዋይነቱን ያስመሰከረበትን፣ በቀዳሚ ጠላቶቹ በይቀሩ በሃገሪቱ አስተዳደር ውስጥ የሚሳተፉበትን መንግሥት መጋቢ አቋቋመ:: ሃገሪቱም ፍጹም ገለልተኛ እንደምትሆን አስታወቀ:: የናዎቹም፣ የሩስያ ተስፋፊዎችን ጠብ ቀው ቢፈሩ ቢቸሩ የመጋቢን መንግሥት አወቁ:: ጦርነቱ ቢቀጥልስቸውማ ኖር ለሩስያ ተስፋፊዎች ጥቅም የኢትዮጵያ ወጣቶች ወደ ዘምባብዌ ዘምተው እንዲያልቁ ተደገበሰቸው ነበር:: ከባዕድ ቅምጥ መንግሥት ከዚህ የተለየ አይጠበቅም::



## 6. ማህበራዊና ባህላዊ ተፅዕኖ

የሩስያ ተስፋፊና ጣልቃ ገብ መንግሥት አገሪቱን በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በወታደራዊ መስኮች እንዴት ከቁጥጥሩ ሥር እንዳዋለ በጥሩ ያበየን ይመስለናል:: ነገር ግን ማንም ሃቀኛ ኢትዮጵያዊ ዜጋ እንደሚያስተውለው፣ ተስፋፊዎቹ በሃገሪቱ ጉዳይ ውስጥ የማይገቡበት ቀዳዳ እንደሌለ ግልጽ ነው:: በዚህ በኩል፣ የሶቪየት ሀብረትን "ሃያልነትና" የሶቪየት ህብረትን "የበላይነት" ለመጋትና፣ የኢትዮጵያ ህዝብ የሃገር ፍቅር ስሜት እንዲላሸቅ ለማድረግ የሚወርደው የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ራሱን የቻለ ክፍል ሆኖ ይመጣል::

ለህዝብ ማስተማሪያ፣ ለሃገር ፍቅር ስሜት ማጠናከሪያ፣ ለዲሞክራሲያዊና ህዝባዊ ትግል መቀስቀሻ መዋል የሚገባቸው የዜና ማሰራጫዎች፣ የትምህርት ተቋሞች፣ ህዝባዊና መንግሥታዊ ድርጅቶች፣ በሃገር ቋንቋዎች የሚሠሩ የሩስያ ተስፋፊዎችና የተቀጢላዎቻቸው አፈ ቀላጤ ሆነዋል::በማርክሲዝም አስታከው የሚለፍፉትም፣የሩስያ ተስፋፊዎችን"ፍጹማዊ የበላይነት "በኢትዮጵያ ህዝብ ህሊና ውስጥ በጉልበት ለመስረፅ እንጂ ሌላ ዓላማ ያለው ጉዳይ አይደለም:: የሶቪየት ሀብረት 'ታላቅነት'፣ የሶቪየትና የተቀጢላዎቿ 'የበላይነት'፣ የመሪዎቻቸው 'አስተዋይነትና ብልህነት' ካልተወደሰ የማይሆነው ለዚህ ነው:: ይህን ከንቱ ውዳሴ ያለዘለ ፅንስ ሃሳብና ንግግርም የማይሰማው ለዚህ ነው:: እንዳውም ግዲታ ነው:: ይህ በ'ገራ' አድርጎ ወደ ዘረኝነት ይጠጋ እንደሁ እንጂ ከወዝአደር ርዕዮተዓለም ጋር የሚያዛምደው ነገር የለም::

የአዲሱን ትውልድ አእምሮ ለመሰለብ፣ ማናቸውም ማህበራዊ አውታሮችና የትምህርት ተቋሞችን በቁጥጥር ሥር ለማዋል ከፍተኛ ዘመቻ ይካሄዳል:: ሃገሪቱን ምሁር አልባ አድርጎ፣ የአሜን ባይ ምሁራንን ትውልድ ለመተካት ዓይን ያወጣ ፀረ ምሁር ዘመቻና ፕሮፓጋንዳ ይካሄዳል:: በዩኒቨርሲቲ አካባቢ የሚገኙ ሃገር ወዳድ ምሁራን "የኢምፔሪያሊስቶች ገርፍ" እየተባሉ የቁም ስቅላቸውን ያያሉ:: በነሱ ፈንታ አፍ ያልፈታ የሶቪየት ሀብረትና የሌሎች ምሥራቅ አገሮች መምህራን እየተተኩ መደነቋቆሩ አነበ፣ ብሄራዊ ይዘት ያለው ትምህርት እንዲጠፋ እየተደረገ ነው:: በዚህ ላይ ደግሞ፣ ከጣሊያን ዘመን ወዲህ ባልታየ ትምክህተኝነትና ዘረኝነት የኩሩውን የኢትዮጵያ ህዝብ ቆሽት እያሳረረ ናቸው:: ህዝቡ ሚስቶቹንና ልጁን "ለዓለም አቀፍ" ፍትወት ማስተናገጃ እንዲያቀርብ እየተገደደ፣ አሳፋሪ የሆነ የውርደትና የፀፀት ታሪክ በመፃፍ ላይ ይገኛል::

እንግዲህ እናጠቃልል፣

መኢሶን ገና በመጋቢት 1969 ዓ.ም. የዚህ ሁሉ ውርደትና ፀረ አብዮት ሽታ ሲጀምር፣ "በዓለም አቀፋዊነት" ስም ከሚደገሰልን ባርነት እንድንገጠን ቀቅና ይህንን ሤራ እንድንቃወም ጥሪ ማቅረቡ ይታወሳል:: በፕሮግራሙ ላይ ሆነ፣ በርሱ ግንባር ተሳታፊነት በተዘጋጀው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ አብዮታችንንም የሚያራምድ፣ ብሄራዊ ነፃነታችንንም የሚያስከብር የገለልተኝነት ፖለቲካ ቀይሶ ተቀምጧል:: እየተቀደደም ነው:: ከዚህ ዓላማው ቅንጣትም ፈቀቅ ባይል ባለፉት በስት ዓመታት በፖለቲካ፣ በፕሮፓጋንዳና በዲፕሎማቲክ መስኮች ከፍተኛ ትግል አካሄዷል:: ሌላው ቀርቶ፣ መኢሶን የውጭ አካል አማካኝነት፣ በተለይ ከኩባና የደቡብ የመን መንግሥታት ጋር በመገናኘት "በኢትዮጵያ በሚካሄደው የአብዮት ቅልበሳ፣ እንደጉርፍ በሚፈሰው የኢትዮጵያ ልጆች ደም በታሪክ ፊትና በዓለም ተራማጆች ፊት ተጠያቂ እንደሚሆኑ ለማስረዳት ከፍተኛ ጥረት ተደርጎ ነበር:: ነገር ግን መኢሶን የተጠየቀው፣ ገለልተኝነትን ትቶ የነርሱን "ዓለምአቀፋዊነት" እንዲቀበል:: በኢትዮጵያ ህዝብ እተማመናለሁ የሚለውን ትቶ፣ እምነቱን ሁሉ "በታላቋ ሶቪየት ሀብረት ላይ እንዲጥል":: የሃቀኛ ተራማጆች ሀብረትን ትቶ የሽለቃ መንግሥትን "ብቸኛ መሪነት" እንዲቀበል፣

ክብሩን ሸጦ ለተስፋፊዎች እንዲያድር ተፅዕኖዎች በተደጋጋሚ ተሞከረውበት ነበር::
የተደረጉት ውዴዴቶችና ውጤታቸው መአበገን በሃገር ፍቅር ስሜት አገ
ዲብረታ አደረጉት አገሯ፣ ለተስፋፊዎችና ለቡችሎቻቸው እንዲያዝበደዱ አስደረጉት
ም:: ወደፊትም ቢሆን፣ ንቅናቄያችን አብዮታችን ገቡን ባይመታ፣ ብሄራዊ ክብራ
ችንን መልሰን ባንጎናፀፍ፣ የውጭ ጠር ከነጓዙና ከነጉትቱ ከኢትዮጵያ ምድር በ
ይወጣ በሬት የትግላችንን ትጥቅ አንፈታም:: ይህ ለተስፋፊዎቹም፣ ለከሃዲዎቹም
ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ ነው:: [illegible] እንዳልነው፣ በዛሬው ወቅት ዋ
ናው ቅራኔ በዛሬው አገዛዝና በሩስያ ተስፋፊ መንግሥት በአንድ ወገን፣ በኢትዮጵ
ያ ሰፊ ህዝብ በሌላው ወገን ነው:: መኢሶን ከኢትዮጵያ ህዝቦች ጎን ተሰልፎ
በትግሉ ይቀጥላል::

## 7. አቋማችን እንደገና

የኢትዮጵያ ህዝቦች ለብሄራዊ ነፃነትና ለህዝባዊ አርነት እስከዛሬ
ያካሄዱት ተጋድሎ በኩራት የሚታወሰውን ያህል፣ ዛሬ ደግሞ በሃፍረት የምንመዘገ
በው ሃቅ አለ:: "በብሄራዊ ነፃነቷ ለዘለሰመ ትኑር" የምንላት ኢትዮጵያችን
በሩስያ ተስፋፊዎች የእጅ አዙር ቅኝ ገዛትነት ..በርነት [illegible]፣ የነርሱ
ቅምጥ በሆነ ወታደራዊ አምባገነን አገዛዝ ሥር [illegible]የሚቀቁጥ ነው:: ከሁሉም በለ
ይ፣ እና ሃቀና ተራማጆችን የሚያንገበግበው ደግሞ ይህ ሁሉ በ"ሶሻሊዝም" ስ
ም፣ ይህ ሁሉ በ"ኮሚዩኒዝም" ስም መሆኑ ነው:: ይሁንና፣ ይህ ብሄራዊ ነፃነ
ትን በብሄራዊ ባርነት፣ ፍትህን በአምባገነንነት፣ ዲሞክራሲን በፋሽስት ቀራጭነት፣
ሰብዓዊ መብትን በሰብዓዊ ስቃይ፣ የብሄረሰቦች ዕኩልነትን በትምክህተኝነት፣ በ
ሰላምን በጦርነት ፣ ህዝባዊ ብልፅግናን በረሃብ በስደትና በጭናና የሚለውጠው
'ሶሻሊዝም' የተስፋፊዎችና የቅምጦቻቸው እንጂ፣ እና ከምናውቀው፣ እና ከምት
ነሰት፣ እና ከምንሰቀለትና የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ በአድናቆት ያልመው ከነበረው
ሶሻሊዝም ጋር የሚያዛምደው አንዳችም ነገር እንደሌለ መታወቅ አለበት::

የሩስያ ተስፋፊዎች "ሶሻሊዝምና ኮሚዩኒዝም"፣ በአደንቋሪ ፕር
ፓጋንዳና በአፍ ባይሆን ዛሬ በሬው የኢትዮጵያ ህዝብ በገሃድ በሚያየው በብሄ
ራዊ ባርነት፣ በፋሽስት ቀራጭነት፣ በስቃይና ገፍ፣ በጦርነትና ዕልቂት፣ በረሃብና
ጭቆና የሚመስለው ነው:: እውነተኛ ሶሻሊዝም ግን፣ ሲማይገለስ ብሄራዊ ነፃነ
ት፣ በብሄረሰቦች ዕኩልነት፣ በዲሞክራሲና በሰብዓዊ መብት፣ በህዝባዊ ብልፅግና
ና በሃገር ዕድገት መሠረት ላይ የሚገነባው፣ የሰውን ተበጭ መበዝበዝ ከሥረ መ
ሠረቱ የሚያስወግድና እውነተኛ እኩልነትን የሚያሰፍነው ነው:: ይህ የታወቀ ጉዳ
ይ ነው:: ይሁንና፣ ተስፋፊዎችና ቅምጦቻቸው በሳሉት የ"ሶሻሊዝም" የጠረመት
ምስል የተነሳ ኢትዮጵያ ለዚህ መብቃቷ ራሱ፣ በኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ንቃተ ህ
ሊና ውስጥ ስለ ሶሻሊዝምና ኮሚዩኒዝም የተዛባ ስዕል /በጭንቅላቱ የሣለ/ እ
ንዲፈጠር ማድረጉ አይቀርም:: ስለሆነም፣ የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ለተቀደሰው ሃ
ቀና ሶሻሊዝም ያለው አድናቆትና አክብሮት ተመልሶ እንዲታደስ ለማድረግ አን
ቢን፣ ራሱን የቻለና ካለፈው ያልነበ መስዋዕትነት የሚጠይቅ እጅግ የተወሳሰበ
ትግል፣ ሃቀና ተራማጆችን ወደፊት እንደሚጠብቃቸው ከአሁኑ መናገር ይቻላል::
ዛሬ ግን ለሁሉም መነሻ የሚሆነው የተገበበው የብሄራዊ ነፃነታችን ጉዳይ አለ::
ከሁሉም አስቀድሞ ኢትዮጵያ ዛሬ ካለችበት ከሩስያ ተስፋፊዎች የባርነት ቀንበር
ና ከቅምጥ መንግሥታቸው ፈሽስት ቀራጭነት ተላቃ "በብሄራዊ ነፃነቷ ለዘለሰመ ት
ኑር" የምንላት መሆን አለባት:: ለዚህ፣ ሃገሩንና ወገኑን አፍቃሪ የሆነ ሁሉ
ለብሄራዊ ነፃነትና ለህዝባዊ አርነት የሚያደርገውን የጋራ ተጋድሎ በቆራጥነት
መቀጠል ይኖርበታል:: የቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው የብሄራዊ ነፃነታችን ጉዳይ
ነው:: የሩስያ ተስፋፊዎች ሃገራችንን ለቀው ይውጡ..

1. ብሄራዊ ነፃነት:— የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነቱንና ክብሩን ለማ
ስጠበቅ በጋደል የኖረና የሚኖር ህዝብ መሆኑ ተብሎ ያለቀ ነው:: ይህ የኢትዮ
ጵያ ህዝብ ሊቀደቅለት የኖረው ብሄራዊ ነፃነት ግን ከአብዮታችን ቅልበሳ ጋር
ተያይዞ በዘመናዊ ባንዳዎችና ከሃዲዎች አማካኝነት የባዕድ ሃይሎች ዕጁ መነሻ
ተደርጉ ተገዐል:: በኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ የተፈናጠጠው ወታደራዊ አምባገ
ነን መንግሥት፣ የሩስያ ተስፋፊና ጣልቃ ገብ መንግሥት ጫማ ላሽ ሆና በቅምጥ መ
ንግሥትነት እያገለገለ፣ ሃገራችን ኢትዮጵያን የብሄራዊ ውርደት ማቅ አከና
ነቧታል:: ይሁንና፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች ደግሞ ይህን የባሰ መሣሪያ ያደረጋ
[illegible]



መኢሶን ለብሄራዊ ነፃነት [illegible] አነዛበመበበረው
ሁሉ ዘረፈ፣ የሃገራችንን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የወታደራዊ ተቋም በቁጥጥራቸው
ሥር አድርገው ኢትዮጵያን በባርነት የሚገዙት የሩስያ ተስፋፊዎች እንደ አሜሪካ
ን ኢምፔሪያሊዝም በቀሉት ከኢትዮጵያ እንዲባረሩ ለማድረግ ትግሉን ይቀጥላል::
መኢሶን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ሆኖ የሚቀደቀው፣ የዛሬዎቹ የቅምጥ መንግሥት በ
ለሟሎች እንዲሁ ለቀረፁት ኢትዮጵያ ባይሆን፣ የማንም ተቀጢላ ያልሆነች፣ ነፃ፣
ዲሞክራሲያዊት፣ ኩሩ፣ የበለፀገችና በራሷ የምትተማመን ህዝባዊት ኢትዮጵያን ለ
መመሥረት ነው:: በማንም የባዕድ ሃይል እንዲገበሰበት ለማይፈቀደው ብሄራዊ ነ
ፃነት፣ መኢሶን ለሃገር ክብርና ለወገን ነፃነት ከሚቆሙ ሃቀና ዜጎች፣ ሃገር ወ
ዳድና ዲሞክራቶች ጋር ጎን ለጎን ሆኖ ተጋድሎውን ይቀጥላል::

2. የብሄረሰብ ጥያቄና የርስበርሱ ጦርነት:— የብሄረሰቦች እኩል
ነት ያለአንዳች ገደብ ታውቆ በሥራ ካልተተረጎመና ካልተረጋገጠ፣ ይህች የአያሌ
ብሄረሰቦች ምድር የሆነችው ውድ ኢትዮጵያችን ከቶም አንድነቷን ልታገኝ አትችልም::
በዕኩልነት በመፈቃቀድና በወንድማማችነት ላይ የተመሠረተች አንድነቷ ከብረት የ
ጠነከረ፣ ህዝባዊትና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያም ልትመሰረት የምትችለው፣ ይህ የ
ብሄረሰቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን እስከመገንጠል ድረስ ያላቸው
የማይገሰስ ዲሞክራሲያዊ መብታቸው ተከብሮ ሲረጋገጥ ብቻ ነው:: በተስፋፊው
የሩስያ መንግሥት እየተደገፈ፣ ቅምጡ ወታደራዊ አምባገነን መንግሥት በጭቁን ብ
ሄረሰቦች ላይ ዛሬ በሚያወርደው ትምክህተኝነት የተነሳ ግን፣ ኢትዮጵያ እውነተ
ኛ አንድነቷን ከቶም ልታገኝ አልቻለችም:: እንዲያውም፣ ወንድማማች ህዝቦች የ
ሚተላለቁበት፣ የተስፋፊዎች የጦር መሣሪያ መፈተሻ፣ የነርሱ ጦር መሣሪያ ማራገ
ፊያ የነርሱ ጥቅም ማካበቻ የሆነ የርስ በርስ ጦርነት በየአቅጣጫው የተስፋፋብ
ት የተበታተነች ሃገር ሆናለች:: በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምሥራቅና በምዕራብ፣ በ
ኢትዮጵያ አራቱም ማዕዘን በኢትዮጵያ ጭቁን ብሄረሰቦች ላይ የሚወርደው የትምክ
ህተኛው ቅምጥ መንግሥትና የሩስያ ተስፋፊዎች ፀረ ጭቁኖች አመፅ መረን ለቋል::
ኢትዮጵያ ብሄረሰቦቿ በነፃና በዲሞክራሲያዊ መንገድ የሚያብቡባት ነፃና ጠንካራ
ኩሩ ምድር ባትሆን፣ የገዛ ብሄረሰቦቿ እንደ ቅጠል የሚረግፉባት፣ በእርስበርስ
ጦርነት የተወጠረች ...በሌላም የሁለቱ ኃያላን መንግሥታት መፋለሚያ ለመሆን የ
ተቃረበች ሃገር ሆናለች::

የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽም፣ በአብዮት ስም ለተቀለበሰ አብዮትና ለ
ፀረ--አብዮት፣ በአንድነት ስም ለመበታተን፣ በብሄራዊ ነፃነት ስም ብሄራዊ ነፃ
ነታችንን ለባዕድ ተስፋፊ ሃይል ለሸጠ ቅምጥ መንግሥት በከንቱ ደሙን የሚያፈስ
ወገን እንዲሆን ተደርጓል:: ቃል ኪዳን ለገባለት፣ በሰላም ብልፅግናና ዕድገት
ለሚታደልበት ህዝባዊት ኢትዮጵያ በመቆም ፈንታ፣ በተስፋፊዎች እየታዘዘና እየተ
ረሸነ የትምክህተኞች ጦርነት እንዲያካሂድ እየተገደደ ነው:: ይሁንና፣ የኢትዮ
ጵያ መለዮ ለባሽ ቃል ኪዳኑ ለብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም እንጂ
ለትምክህተኝነት አይደለም:: ፍላጎቱ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን አባር ብሄራዊ
ነፃነትን ለማስከበር እንጂ፣ የሩስያ ተስፋፊዎችን በርሱ ዕገር ተክቶ ለሌላ ብሄ
ራዊ ውርደት ለመቆም አይደለም:: ፍላጎቱ በሰላም እንጂ፣ የኢትዮጵያ ጭቁን ብሄ
ረሰቦች ላይ ጦርነት ማካሄድ ከቶም አይደለም:: በመሆኑም፣ ቃል ኪዳኑ ለብሄራ
ዊ ነፃነትና ለአብዮት፣ አያም ከጭቁን ብሄረሰቦችና ከኢትዮጵያ ህዝቦች ዲሞክራ
ሲያዊ መብት መከበር ጋር እንጂ ሌላ ሊሆን አይገባም::

ዛሬ በኢትዮጵያ አራቱም ማዕዘን የሚታየው የርስ በርስ ጦርነት
"የበርጉ ገበች ጦርነት፣ የሱማሌ ዐረራ፣ የተገንጣዮች ሤራ...ወዘተ" ተብሎ
በሚያደነቁር መዝሙር የሚታለፍ ጉዳይ አይደለም:: በኢትዮጵያ የሚታየው የርስ
በርስ ጦርነት ምንጭ፣ እንደ ሱማሌ ያሉ ፀረ ኢትዮጵያ የሆኑ ተስፋፊ ሃይሎች
የፈለጉትን ያህል ቢኖሩም፣ የችግሩ ምንጭ በኢትዮጵያ የብሄረሰቦች ጥያቄ ተገቢ
መልሱን አለማግኘቱ ነው:: የቅምጡ መንግሥት ትምክህተኝነት ያስከተለው ጠንቅ
ነው:: የሩስያ ተስፋፊዎች ለሚያካብቱት ጥቅም ሲሉ ኢትዮጵያን ማስቀያ የሌለው
ጦርነት ውስጥ ለመክተት መፈለጋቸው ነው:: የሩስያ ተስፋፊዎች ኢትዮጵያን በቁ
ጥጥራቸው ሥር አድርገው በብሄራዊ ባርነት መግዛታቸው ነው:: ኢትዮጵያና የኢት
ዮጵያ መለዮ ለባሽም በሰላም የሚያገኙት ትምክህተኛው ቅምጡ መንግሥት
በጭቁን ብሄረሰቦች ላይ ያወጀው ጦርነት ሲቆምና የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች [illegible]

መኢሶን፣ ተስፋፊዎችና ቅምጥ መንግሥታቸው በጭቁን ብሄረሰቦች ላይ የሚያወርዱትን ጭፍጨፋ እያወገዘ፣ ይህ መብታቸው እንዲከበር ያላሰለሰና የማያወላውል ተጋድሎውን ይቀጥላል:: መኢሶን፣ ይህ ለሩስያ መንግሥት ጥቅም ማካበቻ በቅምጥ መንግሥታቸው የሚካሄደው የርስበርስ ጦርነት እንዲቆም፣ መብታቸው ከተረገጠና ከሚጠፈጠፉት ጭቁን ብሄረሰቦች ጎን በመሆን እየታገለ፣ ሰላም ለኢትዮጵያ መሰዋ ሰበብ እንዳይወርድ፣ ሰላም በኢትዮጵያ እንዲሰፍን፣ ብሎም ብሄራዊ ነፃነቷ የተከበረና ብሄረሰቦቿ በዕኩልነት የሚኖሩበት አንድነቷ ከብረት የሚጠነክር፣ ሰላማዊት፣ ኩሩና የበለፀገች ኢትዮጵያ እንድትታነፅ ይታገላል::

3. ፍትህ፣ ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብት:— በራሱ ሃገርና በራሱ ህዝብ ላይ ዲሞክራሲን አፍኖ በአምባገነንነት የሚገዛ፣ የገዛ ህዝቡን ሰብዓዊ መብት ረግጦ በጭካኔ የሚገዛ የባዕድ ሃይል — /ሶቭየት ህብረት ከአርጀንቲና ጋር ሰብዓዊ መብትን በመድፈር ከመጀመሪያዎቹ ሦስት የዓለም አገሮች አንዷ ናት/ — ቅምጥ ከሆነ መንግሥት ጌታው ከሆነው የተለየ ይሆናል ተብሎ አይጠበቅም:: የሩስያ ተስፋፊዎች በሃገራችን ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንደጀመሩ አብዮታችን እየተቀለበሰ የመጣውን ያህል፣ ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶችም በቅምጡ መንግሥታቸው ያንኑ ያህል እየተረገጡ፣ ዛሬ በፀረ ዲሞክራሲ፣ በፀረ ርትዕና በኢ—ሰብዓዊ አየር ውስጥ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ታፍኗል:: ታጋይ የኢትዮጵያ አብዮታዊ ልጆች በመቶ ሺህ ያለቁትን ያህል በብዙ ሺህ በየእሥር ቤቱ ታጉረው ፍጹም ኢ—ርትዕና ኢ—ሰብዓዊ ስቃይ እየደረሰባቸው ነው:: በነዚሁ በሩስያ ተስፋፊዎችና ተቀጥላዎቻቸው፣ በኢ—ሰብዓዊነት የሰለጠኑትና ዘመናዊ በሆነ የጭካኔ ዘዴ በተካኑት፣ በነርሱ አማካሪዎች አማካኝነት መሠረታዊ የሰው ልጅ መብት በኢትዮጵያ ተረግጦ ይገኛል:: ፍትህ ተጥሏል፣ ዲሞክራሲና ሰብዓዊ መብት ተረግጧል::

መኢሶን፣ የሩስያ ተስፋፊዎችና ቅምጡ መንግሥታቸው በኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ላይ የሚያወርዱትን ኢ—ርትዕና ኢ—ሰብዓዊነት እያጋለጠ፣ የፖለቲካ እሥረኞች ያለአንዳች ገደብ እንዲለቀቁ ይጣገላል:: በአጠቃላይ ለፍትህ፣ ለሰብዓዊና ለዲሞክራሲያዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ ያለ አንዳች ገደብ መከበር ያላሰለሰ ትግሉን መኢሶን ይቀጥላል::

4. የደቀቀና የዘቀጠ የኑሮ ሁኔታ፣ ረሃብና ችግር:— የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ አብዮቱን ያካሄደው ከ5 ሚሊዮን የሚበልጡ ወገኖቹ በረሃብ አንጓያልቶ፣ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖቹ ከውድ እናት ሃገራቸው ተሰደው በሰው ሃገር በደተቀር ሆነው እንዲኖሩና መላው የኢትዮጵያ ህዝቦች በችጋርና በስቃይ ውስጥ እንደዘረረው እንዲማቀቁ አልነበረም:: ይሁንና፣ አብዮቱ የተቀለበሰበት፣ ብሄራዊ ነፃነቱ ከተራብ ህዝብ መንጋጋ ባቦ /ሰንጊ/ በሚነጥቅ ተስፋፊ መንግሥት የተገበበት፣ በህዝባዊና በዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ፋንታ ፀረ ዲሞክራሲያዊ፣ ወታደራዊና የባዕድ ሃይል ቅምጥ የሆነ መንግሥትን ያተረፈ ህዝብ ዕጣው ይሄው ነው:: ወዘአደሩ፣ ገበሬው፣ ከተሜው፣ በጠቅላላው መላው የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ በረሃብና በችጋር እየተጠበሰ ነው::

በጀግናው ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብና በግንባር ቀደም ልጆቹ ትግል የተገኘው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም አንደኛው ዓላማ፣ የሰፊውን ህዝብ ኑሮ ማሻሻል ነበር:: ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ስሚካሄድበት ሃገር ውስጥ ደግሞ የሰፊውን ህዝብ ኑሮ ለማሻሻል የተተለሙ ዓላማዎች ለዘንተ ዓለም የተነደፉ፣ ወደጎን ቅምጦች መመፃደቂያና ለግድግዳ ጌጥ ቸው የታሰቡ ባይሆኑ የቅርብ ጊዜ ዓላማዎች ናቸው:: መለስተኛ ፕሮግራም የሚባለውም ለዚሁ ነበር:: ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዓላማዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ደግሞ፣ አርሶ አደሩ የመሬቱ ባለቤት ሆኖ የሥራ ፍሬውን ይጠቀምበታል በሚለው መልክ እንዲገለገልበት፣ ወዘአደሩ የሥራ መብቱ ተጠብቆ እንደሥራው የጉልበቱ ዋጋው እንዲከፈለው፣ ነጋዴው ሥርዓት ባለው መንገድ በተመጠነለት መስክ ተሰማርቶ እንዳያባድግ፣ ብሄራዊ ከበርቴው የጭቁ ኢምፔሪያሊስት ተፅዕኖ ታግዶለት ለሃገር ብልፅግና እንዲሠራ፣ ነዋሪና የቀረው የህብረተሰብ ክፍል እንደሥራው የአገልግሎቱን ፍሬ እንዲያገኝ፣ ...... ወታደሩ በሰላም አገር ብሄራዊ ነፃነትን ከመንከባከብ ባሻገር በምርት ሥራ ውስጥ እየተሳተፈ የሃገር ኢኮኖሚን እንዲያዳብር፣ የእርሱም ኑሮ እንዲሻሻል ...ወዘተ ነበር:: ይሁንና፣ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱ የተቀለበሰበት ህዝብ፣ የባዕድ ቅምጥ መንግሥት የተጫነበት ህዝብ ግን ሌላ መሆኑ የታወቀ ነው::



አርሶ አደሩ ያተረፈው የአርሾ መሬቱን በተስፋፊዎች መንግሥት ...፣ በጦርነት እየተገፋ መሬቱን መልቀቅና መሰደድ፣ ወዘአደሩ ያተረፈው በባርነት ደመዝ የሥራ ጉልበቱን መሸጥና በብዙ ሺህ ወደ በዘኔነት ማሽቆልቆል፣ ነጋዴውና ብሄራዊው ከበርቴ ያተረፉት የተስፋፊ መንግሥት ከበርቴ አዲስ ተፅዕኖና የርሱ አልባሌ ሸቀጣ ሸቀጦች መራገፊያ መሆን፣ ነዋሩ ..ሌላው የህብረተሰብ ክፍል ያተረፈው በ"ኤክስፐርትነት" በአማካሪነት" በወዘተ ስም የሚጎርፉት ተስፋፊዎችና የቅምጡ መንግሥት ሎሌነት ... መለዮ ለባሹ ያተረፈው የፀረ ብሄራዊ ነፃነት ሃይሎች ቅጥረኛና ታዛዥ መሆን፣ በባዕድ ወታደሮች እየተነዳና ከጀርባው እየተረሸነ በገዛ ወገኖቹና በኢትዮጵያ ጭቁን ብሄረሰቦች ላይ ጦርነት ማካሄድ ሆና አናገኘዋለን::

አብዮት ከተቀለበሰና አዲስ በዝባዥና ጨቋኝ መደብ በአንድ ህዝብ ላይ ከተንሰራፋ፣ የአንድ ሃገር ብሄራዊ ኢኮኖሚ በባዕድ ሃይል ከተመዘበረ —ያውም የዚህ ባዕድ ሃይል ቅምጥ መንግሥት የፖለቲካ ሥልጣን ጨብጦ ከተደላደለ— ረሃብና ችግር ተወግዶ ህዝባዊ ብልጽግናና ዕድገት ከቶ ሊተካ አይችልም:: ማለትም፣ የዓለም ህዝቦችን ለመመዝበር ገና አዲስ የሆነው የሩስያ ተስፋፊ መንግሥት ኢትዮጵያን በቁጥጥር ሥር አውሎ እንዳሻው እየረገጠ፣ ገና በልቶ ያልጠረቃ የመሰለው አዲስ የተደላደለው የተስፋፊዎቹ ቅምጥ ወታደራዊ አምባገነን መንግሥት በኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ እየጨፈረ፣ ረሃብና ችግር ከኢትዮጵያ ተወግደው ህዝቡ ከአዘቀጠና ከደቀቀ ኑሮ ተላቆ ብልጽግናና ዕርምጃ ሊሰፍን ይችላል ማለት ዘበት ነው:: መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ ከገባበት ረሃብና ችግር ለመላቀቅና ከበጠመበት የኑሮ ረመጥ ለመውጣት እንደየካቲቱ ከዳር እስከዳር ተነስቶ እነዚህ ሁለት ቀንደኛ ጠላቶቹን ማስወገድ ይኖርበታል::

መኢሶን ለእያንዳንዱ የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ዓላማዎች የተቀደቀውን ያህል፣ ዛሬም ሆነ ወደፊት ሁለቱ ቀንደኛ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶችን—የሩስያ ተስፋፊዎችንና ቅምጡ መንግሥታቸውን በግንባር ቀደምትነት እየታገለ ለሰፊው ህዝብ ኑሮ መሻሻል ይታገላል::

ባጭሩ፣ አንደኛ፣ መኢሶን በማንም ሃይል ለማይናወጸው ብሄራዊ ነፃነት፣

ሁለተኛ፣ መኢሶን ለሰላምና ከራሳቸው ከጭቁን ብሄረሰቦች ሌላ ማንም ለማያዝበት የተሟላ የብሄረሰቦች ዕኩልነት፣

ሦስተኛ፣ መኢሶን ለፍትህ፣ ለዲሞክራሲና ለሰብዓዊ መብቶች ያለአንዳች ገደብ መከበር፣

አራተኛ፣ መኢሶን ለሰፊው ህዝብ ኑሮ መሻሻል፣ ለኢትዮጵያ ብልፅግናና እርምጃ አብዮታዊ ተጋድሎውን ይቀጥላል::

5. የትግል አንድነት ጥሪ:—

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ነፃነትና ክብር ጉዳይ፣ የኢትዮጵያ ሰላምና የብሄረሰቦች እኩልነት ጉዳይ፣ የዲሞክራሲ የሰብዓዊ መብትና የፍትህ ጉዳይ፣ የኢትዮጵያ ብልፅግናና እርምጃ ጉዳይ መቼም ሆነ ዛሬ የመኢሶን ብቻ አልነበረም:: አይደለም :: ሥልጣን ካሰከራቸው ጥቂት ከሃዲያን በስተቀር፣ ክብራቸውን ና ክብራችንን ሽጠው የባዕድ ቅምጥ ሆነው ከሚያገለግሉ የሃገር ደላሎች በስተቀር፣ የተስፋፊዎቹና የወታደራዊው ቢሮክራሲያዊው መንግሥት ጥቅም ተካፋይ ከሆኑ ታላላቅ የሚሊተሪ /ሲቪል ቢሮክራቶችና ቴክኖክራቶች በስተቀር፣ የኢትዮጵያን ህዝብ በሙሉ የሚመለከቱ ናቸው:: እንዲያውም፣ በተለይ ዛሬ፣ ሃገራቸውን የሚወዱና በተስፋፊዎችና በቅምጦቻቸው የሚበሻቀጡት ኢትዮጵያውያን ሁሉ የሚመለከቱ ጉዳዮች ሆነው ቀርበዋል::

አሰላለፉም ግልጽና አጭር ነው:: ለብሄራዊ ባርነትና ውርደት የቆሙ ቅምጦችና ተስፋፊዎች በአንድ በኩል፣ ለብሄራዊ ነፃነት፣ ክብርና ሞገስ፣ ለኢትዮጵያ ሰላምና ብልፅግና የቆመ ህዝብ በሌላ በኩል ነው::

የመኢሶን የትግል ጥሪም አጭር ነው::

በሩስያ ተስፋፊዎችና በቅምጦቻቸው የተቀጣ ሃይል ሁሉ እነዚህ ጥያቄዎችን አንግቦ በአንድነት የጋራ ክንዱን ማንሳት አለበት:: መኢሶን ለነዚህ ጥያ

ሃገር ወዳዶችና አርበኞች ጋር — አልፎም ከማንም አገራቸውን ከሚወዱ ኢትዮጵያዊያን ጋር ለመተባበር፣ ድርጅታዊ የትግል አንድነት ለመፍጠርና ለመታገል ዝግጁ ነው::

## የመኢብን ጥሪ የማያሻማ ነው::

በዘረኛ የባዕድ መኮንኖች እየተመራ፣ እነሱ ባስታጠቁት መሣሪያ ኢትዮጵያዊያን ወገኖችን መጨረስ ያስቆጣው መለዮ ለባሽ፣ ነጋ ጠባ የሃገሪቱን ክብርና ጥቅም ገደል የሚከት የባህል፣ የኢኮኖሚና የንግድ ውሎችን እየታዘዘ መፈራረም ያንገበገበው ባለሥልጣን፣ በባዕዳን ትጥቅ የናጠጡ ከሃዲያን የጪኸት ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ያንገፈገፈው ሰፊው ህዝብ፣ የሃገሩ ብሄራዊ ነፃነት መደፈር ያስቆጣው አገር ወዳድ፣ ለመብቱና ለእኩልነቱ በተከራከረ የተስፋፊዎች ጥይት ማብረጃ የሆነው የጭቁን ብሄረሰብ ታጋይ፣ ተስፋፊዎች አቅፈው ደግፈው ባጠናከሩት ፀረ—አብዮት ዱላዎችን ሁሉ የተቀማው ወዝአደር፣ ዘረኞቹ ሃገሪቱን አራቁተው በሃገራችን ታሪክ ተሰምቶ ታይቶ ለማይታወቅ ረሃብና ቸነፈር የተጋለጠው ገበሬ፣ የተስፋፊዎች ጥይትና በምብ ስንዝር መሬት እየነሳው በሚሊዮን እየተቆጠረ ለስደት ለመከራና ለውርደት የተጋለጠው ኢትዮጵያዊ፣ ክብሯንና ሰውነቷን ለአዳዲስ መጤዎች ዘረኞች ማስተናገጃ እንድታቀርብ የተገደደችው ኢትዮጵያዊት፣ የከሃዲዎች ዘቀቱና ስነ—ልቡና "ለተለየ" ዘመቻ ያጋለጠው ምሁር ....ወዘተ..ወዘተ. ተባብረው አቋቸውን ማገስት አለባቸው:: አገራቸውን ከጥፋትና ከባሰ ውድቀት ማዳን አለባቸው:: የሃገር ፍቅር ስሜታቸውን አስተጋግዘው በአንድነት መታገል አለባቸው:: አለያም የባሰ ውድቀት፣ የባሰ ድቀት፣ የባሰ ውርደት ነው::

ንብዝ:: ደግሞም እንደ መገንዘብ ያለብን ሃቅ አለ:

ዛሬ የሃገራችን ብሄራዊ ነፃነት ብቻ ሳይሆን፣ ህልውናዋ ራሱ ከጥያቄ ውስጥ የገባበት ወቅት ነው:: የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና የሩሲያ ተስፋፊዎች እንደካምቦዲያና እንደአፍጋኒስታን የአዳዲስ ጦር መሣሪያዎች መፈተሻና መፋለሚያ እያደረጉን ነው:: የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም "ኢትዮጵያን ለማስመለስ"፣ በአካባቢው የነበረውን የበላይነት መልሶ ለማግኘት ከፍተኛ ዝግጅት እያደረገ ነው:: ለዚህም በሶማሊያ፣ በኬንያ፣ በኦማንና በግብፅ የሚያደርገው የጦር ከምችት በቂ ማስረጃ ነው:: ተስፋፊው የሩሲያ መንግሥት ደግሞ፣ "የመከላከያ" ዝግጅቱን በየመንና በኢትዮጵያ እያጠናከረ ነው:: በቀይ ባህር የኢትዮጵያ ደሴቶችና ወደቦች ላይ የባህር ጦር ሰፈሩን መሥርቷል:: በመሃል ሃገርም፣ በሁርሶና በበተርጠሊ / ጊቤ ወንዝ አካባቢ/ የጦር ማከማቻ ሠፈር እንዳሠራ ከሃዲዎች እንደፈቀዱለትና አገር ከልለው እንደሰጡት የታወቀ ነው:: በዚህ ባቢያ፣ ሃገራችን የሁለቱ ሃያላን መንግሥታት የጦር አውደማ የምትሆንበት ጊዜ ሩቅ አይደለም:: ያኔ፣ ስለ ብሄራዊ ነፃነት ቀርቶ ስለህልውናችንም መናገር አንችልም::

እንግዲህ ሁኔታው እንደዚህ አሳሳቢና አስፈሪም ነው:: በሌላው በኩል፣ እና የሃገር ፍቅር ስሜት የሚያንገበግበን ሃይሎች፣ ጊዜው በሚጠይቀው መልክ ተባብረንና ተያይዘን ገና አልተነሳንም:: ይህን እስካላደረግን ድረስ ደግሞ፣ ወደ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ህልውናችን ወደ ውጭ ብሄራዊ ነፃነታችን ተከብሮ ልንኖርበት የምታስችለንን ኢትዮጵያ ለመፍጠር አንችልም::

መኢብን ያለመበልቸት ለኢትዮጵያ ዴሞክራቶች፣ ሃገርወዳዶችና የብሄረሰብ እንቅስቃሴዎች ሁሉ የአንድነት ግንባር ጥሪ አድርጓል:: በዚህ ዐቅሙም የሚያደብው የትግል አንድነት ጥሪ የዚሁ አካል ነው:: የዚህ ግንባር ጥያቄ በየዕለቱ ይበልጥ አንገብጋቢ እየሆነ እንደመጣ ያለፉት ዐራት ሁኔታ በግልጽ ያሳየናል:: መኢብን አሁንም ደግሞ ደጋግሞ የሚለው፣ ለብሄራዊ ነፃነት፣ ለዴሞክራሲና ለብሄረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ሃይሎችን እናስተባብር ነው:: ለዛሬው ሁኔታ መፍትሄው ሃቀኛ ተራማጆች፣ ሃገር ወዳዶች፣ ዴሞክራቶችና የጭቁን ብሄረሰብ ታጋዮች በአንድነት የሚመሰርቱት ሰፊ ህዝባዊ ግንባር ብቻ ነው::

ለብሄራዊ ነፃነት !
ለዴሞክራሲ ለፍትህና ለሰብዓዊ መብት:
ለብሄረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት:
ሰፊ ህዝባዊ ግንባር ...